# ትምህርት አሥር

## አንደኛ ቀን፡-

«እስኪ አንድ መንፈሳዊ ኮንፍረንስ እናዘጋጅ፣» አለ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ። ሽማግሌዎቹ በዚህ አሳብ ላይ ከተወያዩ በኋላ ከጥር 27-29 ኮንፍረንስ ለማካሄድ ወሰኑ። ከዚያ በኋላ ሽማግሌዎቹ ስለ ሌሎች ጉዳዮች ሲነጋገሩ ቆዩ። ጊዜ በርሮ ደረሰና እነሆ ጥር 14 ሆነ። ኮንፍረንሱ ሲጀመር 10 ቀናት ብቻ ነበሩ የቀሩት። ይህም የሽማግሌዎቹን ለብሳቢ አስጨነቀው። በፍጥነት ሽማግሌዎቹን ሰብስቦ፣ «ማንን ነው ለኮንፍረንሱ ተናጋሪነት የምንጋብዘው? ኳየሩስ የትኛው ቢሆን ይሻላል? የምግብስ ጉዳይ? ስንት ብር ይበቃ ይሆን? ገንዘቡስ ከየት ነው የሚመጣው?» ሲል አፋጠጣቸው። ሽማግሌዎቹም አያሌ አማራጮችን አቀረቡለት። በቀጣዩ ዕለት ሰብሳቢው ለእያንዳንዱ የኮንፍረንሱ ተናጋሪና ኳየሮች ስልክ በመደወል ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው መጥተው እንዲያገለግሉ ጠየቃቸው። ነገር ግን አብዛኞቹ በሌሎች አገልግሎቶች ተይዘው ነበር። በመጨረሻም፣ ብዙም የማይታወቅ አንድ ተናጋሪና የአንድ ቤተ ክርስቲያን የ«ለ» ኳየር ለመምጣት ተስማሙ። ለምግብ የተመደበ ገንዘብም አልነበረም። ሰብሳቢው ከወንጌላውያን ደመወዝ ገንዘብ አውጥቶ ለምግብና ተጋብዘው ለመጡት አገልጋዮች የትንራስፖርት መክፈያ አዋለ። ወጣቶችን ሰብስቦ ለዳስ መሥሪያ የዘንባባ ቅጠሎችንና አጠናዎችን እንዲያመጡ ነገራቸው። ነገር ግን ጊዜው የማጠቃለያ ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ በመሆኑ፣ ብዙዎቹ ይህንን ሥራ ለማከናወን አልተመቻቸውም። የምግብ ዝግጅቱን የሚከታተል ሰው ስላልተመደበ፣ ኮንፍረንሱ እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ ጤፉ አልተፈጨም፣ ሲጡም አልተቦካም ነበር። ሰዎች የኮንፍረንሱን የመጀመሪያ ክፍል ለመስማት በሚመጡበት ሰዓት እንኳን መሪዎች ብዙ ነገሮችን ለማደራጀት ይሯሯጡ ነበር። ለተናጋሪውም ሆነ ለኳየር አባላት የመኝታ ቦታ ያዘጋጀላቸው ሰው አልነበረም። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወጣቶች ኮንፍረንሱን መከታተላቸውን ትተው ወደ ጫፌ በመሄድ አገልጋዮቹ የሚተኙ በትን ሣር ማጨድ ጀመሩ። ለዝግጅት የሚበቃ ጊዜ



ስላልነበራቸው፣ ለባኪውም ሆነ ኳየሩ በሚገባ ለማገልገል አልቻሉም ነበር። መሪዎቹ እስከ ኮንፍረንሱ ሁለተኛ ቀን ድረስ ገና ዝግጅታቸውን ስላላጠናቀቁ፣ ቁጭ ብለው እግዚአብሔር የሚናገረውን ቃል ለመስማት አልቻሉም ነበር። ሕዝቡ በዚህ ትርምስ ስለ ተናደዱ፣ ለመባ ብዙ ገንዘብ ለመስጠት አልፈለጉም። ለኮንፍረንሱ የወጣው ወጪ ከመባው ከተገኘው ገቢ ስለ በለጠ፣ ተጨማሪ ገንዘብ ለወንጌላውያን ደመወዝ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ተወሰደ። ኮንፍረንሱ ሲጠናቀቅ፣ ሁሉም ሰው ዝሎ ነበር። «እንግዲህ የወንጌላውያንን ደመወዝ የምንከፍለው ገንዘብ ከየት አምጥተን ነው?» ሲሉ መሪዎቹ ተጨነቁ።

> 1ኛ ጥያቄ: ሀ) መሪዎች ተመሳሳይ ውሳኔ ሲወስኑና ነገር ግን ለወሰኑት ነገር ጥሩ ዕቅድ ሳያወጡ ሲቀሩ የተመለከትህበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) የዕቅድ ድክመት የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው? ሐ) ያለ በቂ ዕቅድ አንድን ነገር ማድረግ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል ወይስ አያስደስተውም? መልስህን አብራራ። መ) ሕዝቡ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ታቅደው ቢሆን ኖሮ ያገኙት የነበረውን ያህል በረከት አግኝተዋል? ለምን? ሠ) ሽማግሌዎቹ ለማድረግ የፈለጉትን ነገር በግልጽ ቢያውቁና ጥርት ያሉ የአፈጻጸም ደረጃዎችን ቢከተሉ ኖሮ እንዴት የተሻለ ኮንፍረንስ ለማካሄድ ይችሉ እንደ ነበረ ግለጽ።

ሽማግሌዎቹ መንፈሳዊ ኮንፍረንስ ለማካሄድ በፈለጉ ጊዜ የተበላሸው ምን ነበር? ነገሩ የተጀመረው ግልጽ ባልሆነ «ራእይ» ነበር። የኮንፍረንሱ ዓላማ ምን ነበር? መንፈሳዊ መነቃቃት ማምጣት ነበር? የታመሙትን መፈወስ? ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መስጠት? ከቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎቶች ለአንዱ ገንዘብ ለማሰባሰብ እየሞከሩ ነበር? ለማድረግ የምንፈልገውን ነገር በትክክል ካላወቅን፣ ግልጽ ያልሆነ ራእይ በአመዛኙ ውጤታማ ያልሆነ አገልግሎት እንድንሰጥ ያስገድደናል፡

ከዚህም በላይ፣ ሽማግሌዎቹ ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት አልቻሉም ነበር። መሪዎቹ እስከ መጨረሻው ድረስ ምንም ሳይሠሩ ነበር የቆዩት። ኮንፍረንሱ እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ ይጠናቀቅ ዘንድ መደረግ የነበረባቸውን ዋና ዋና ነገሮች አላደረጉም ነበር። ስለሆነም፣ ነገሮች ያልታቀዱና ፈር የለቀቁ በመሆናቸው

ሽማግሌዎቹ ተጨነቁ፣ ሕዝቡም ተከፋ:: እግዚአብሔር ጥሩ ዕቅድንና ጥሩ ራእይን ያከብራል::

**ሁለተኛ ክህሎት:- የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ ጥሩ ዕቅዶችን ማውጣት**

የቻይናውያን ምሳሌያዊ አነጋገር እንደሚነግረን፣ «ሺህ ኪሎ ሜትር በአንድ እርምጃ ይጀመራል::» በተመሳሳይ መንገድ፣ በግል ደረጃና እንደ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም የተለያዩ ደረጃዎችን መከተል ይኖርብናል:: እንደ መሪዎች ዋንኛውን ግብ ካወቅን በኋላ፣ ራእዩን እውን ለማድረግ የሚያስችሉትን ደረጃዎች ማዘጋጀት አለብን:: እስከዚህ ደረጃ ድረስ፣ ራእዩ አሳብ ብቻ ነበር:: መጀመሪያ በአእምሯችን ውስጥ ነበር ማሳደግ የጀመርነው:: ራእዩን በአእምሯችን ውስጥ የምናጠናቅቀው ግልጽ ዕቅዶችን በማውጣት ነው:: ከዚያ በኋላ ወደ እውነታ በመቀየር ራእያችንን ለሁለተኛ ጊዜ መገንባቱ ቀላል ነው:: ይህንኑ በጥሩ ሁኔታ ለማከናወን ራእዩን ለመፈጸም የሚያስችሉ ግልጽ ዕቅዶች ማውጣት አለብን:: የነደፍነው ዕቅድ ግልጽና ዝርዝር ከሆነ፣ ብዙ ገንዘብና ጊዜ ሳናባክን ራእዩን ልንፈጽም እንችላለን::

| |
|---|
| 2ኛ ጥያቄ:- በርካታ መሪዎች ለማከናወን ለሚፈልጓቸው ነገሮች ጥሩ ዕቅዶችን የማያውጡት ለምን ይመስልሃል? |

**ዕቅዶችን ስለ ማውጣት ለዎች የሚያስቧቸው የተሳሳቱ አመለካከቶች**

በቁርጠኝነት ዕቅዶችን ለማውጣት እንድንችል ብዙ ክርስቲያኖች ዕቅድ ማውጣትን በተመለከተ የሚያስቧቸውን የተሳሳቱ ነገሮች መረዳቱ ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ ያህል:-

*1. «ነገሮች በፍጥነት ስለሚለዋወጡ፣ ዕቅድ ማውጣቱ ጊዜ ማባከን ነው:: ዕቅድ ካወጣን በኋላ፣ አንዳች ያልተጠበቀ ነገር ስለሚመጣ ዕቅዱን መቀየር አለብን:: ስለዚህ እስከናካቴው አለማቀዱ የተሻለ ነው::» ይህ በመንገድ ላይ ሊገለበጥ፣ ጎማው ሊፈነዳ ወይም የሆነ ያልተጠበቀ ችግር ሊከሰት ስለሚችል በአውቶቡስ ለመሄድ አልፈልግም የማለትን ያህል የሞኝነት ንግግር ነው:: ዕቅድ*



*አላወጣም የሚል ሰው የሚሄድበትን አገር ሳያውቅ፣ ለንት ብር እንደሚበቃው ሳይገነዘብና የሚሄድበት አገር ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ፣ ወዘተ. . . ሳያውቅ ወደ አውቶቡስ ተራ ሄዶ ትኬት እንደሚገዛ ሰው ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሆነ ቦታ ሊሄድ ቢችልም፣ መድረሻው የት እንደሚሆን አያውቅም:: ዕቅድ ካላወጣን፣ ወዴት እንደምንሄድ ወይም መቼ ከምንፈልገው ስፍራ እንደምንደርስ ልናውቅ አንችልም::*

*2. «ዕቅድ ለማውጣት ጊዜ የለኝም:: እያንዳንዱን ሰዓት የማጠፋው በአፋጣኝ የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች ላይ ነው:: ሰዎች እርስ በርሳቸው ይጣላሉ:: ድሆች ገንዘብ ይፈልጋሉ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ አገልግሎቶች ሰላሉ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ዕቅድ ለማውጣት ጊዜ የለኝም::»* ዕቅድ ለማውጣት ጊዜ ያጠረው መሪ፣ ራእይ ያለው አመራር የማይሰጥ መሪ ነው:: የቤተ ክርስቲያኒቱን አዳፊ ጣነገሮች በማስተናገድ ላይ ስለሚሆን፣ ቤተ ክርስቲያን የምትሄድበት አቅጣጫ ስለሌላት፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያህል ልታድግ አትችልም:: ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች ምላሽ በመስጠት ላይ የሚያተኩር መሪ ሁልጊዜም ጊዜ የሌለውና የተዳከመ ከመሆን አያመልጥም:: ለዚህም ምክንያቱ ለሚገጥሙት ችግሮች መሠረታዊ መነሻ ስሆኑት ነገሮች መፍትሔ ስለማይሰጥ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ መሪ በእህሉ ውስጥ የሚበቅሉትን አረሞች ቅጠል ብቻ እየበጠሰ ከሥር ነቅሎ እንደማይጥል ገበሬ ነው:: ከሥር ነቅሎ ስለማይጥላቸው፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ለማረም ይገደዳል:: ጥሩ ዕቅዶችን ማውጣት መጀመሪያው ላይ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም፣ በኋላ ግን ሥራ ያቃልላል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያደናቅፉትን መሠረታዊ ችግሮች ይቀርፋልና::

ለምሳሌ ያህል፣ አማኞች የሚጣሉት ከመንፈሳዊነት ጉድለት ነው:: ሰዎች መጣላታቸውን እንዲያቆሙ ለማድረግ የምንችለውን ያህል ጥረት ልናደርግ እንችላለን:: በዚህም ጊዜያዊ ውጤት ልናገኝ እንችላለን:: ነገር ግን ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እስካልሆኑ ድረስ መጣላታቸው የማይቀር ነው:: መፍትሔ የሚገኝ

ው ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የረዳናቸው እንደ ሆነ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ መጣላታቸውን ያቆማሉ። ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት ማቀድ መጀመሪያ ጊዜ የሚወስድ ሥራ መሆኑ አይካድም። ነገር ግን ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ስንረዳቸው፣ በአማኞች መካከል ያሉት የግንኙነት ችግሮች ይቀረፋሉ። ይህም የኋላ ኋላ ጊዜ ይቆጥብልናል።

*3. «ማቀድ የእኔ ሥራ አይደለም። እኔ የምሠራው መሪዬ የሚነግረኝን ብቻ ነው።»* እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ሁለት ነገሮችን ይዘነጋል። *በመጀመሪያ*፣ ሌሎች ለእኛ ዕቅድ እንዲያወጡ መጠየቅ ማለት እግዚአብሔር የሚሰጠንን ምሪት አናዳምጥም ማለት ነው። እርሱ የሰጠንን አእምሮም አልተጠቀምንም ማለት ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ለክብሩ የሚውሉ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን ስለ ሰጠን፣ እነዚህን ስጦታዎችና ችሎታዎች እንድንጠቀም ይጠይቀናል። እግዚአብሔር ከሰጠን ስጦታዎች አንዱ የማቀድ ችሎታ ሲሆን፣ ይህም በአገልግሎታችን ልዩ ውጤት ያስገኛል። *ሁለተኛ*፣ የሚመራንና የሚያስደስተን ዕቅድ አካል ካልሆንን፣ ችሎታችንን በሚገባ ልንጠቀም አንችልም። ለአገልግሎቱ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ አንሰጥም። ትንሽ ብቻ በመሥራት፣ ሰዓቱ ሳይደርስ በመውጣት፣ መሪው በአጠገባችን በሚኖርበት ሰዓት ብቻ በመሥራት፣ ወዘተ. . . ሥራውን እንበድላለን።

ምንም እንኳን የምንሠራው ከቤተ ክርስቲያን መሪ ክትትል ሥር ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ለግላችንና ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ግቦች አንድ ዓይነት ናቸው ወይ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር ወንጌላዊ እንድሆን ከጠራኝና፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ሥራዎችን እንዳካሂድ ብትፈልግ፣ ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለሴተኛ አዳሪዎች ወንጌል እንድሰብክ ጠርቶኛል የሚል እምነት እያለኝ፣ ቤተ ክርስቲያን ይህ አገልግሎት አሉታዊ አመለካከትን ያስከትላል በሚል ፍርሃት ጥሪዬን ባትቀበል፣ ልወስዳቸው የምችላቸው አራት አማራጮች አሉ።



*በመጀመሪያ*፣ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለሕይወቴ የሰጠውን ጥሪ እንዲቀበሉ እንዲረዳቸው እየጸለየሁ ልጠብቅ እችላለሁ። ዳዊት እግዚእብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚመራ የሰጠው ራእይ እውን እንዲሆንለት ለ20 ዓመታት በትዕግሥት ጠብቋል።

*ሁለተኛ*፣ እግዚአብሔር በሕይወቴ የሚመራኝ ነገር ከቤተ ክርስቲያን አሳብ ጋር እንዲስማማ የራሴን ራእይ ላሰፋው እችላለሁ። ለሴተኛ አዳሪዎች ወንጌል የመስበክ ራእይ የሌላቸውን ሽማግሌዎች ከመውቀስ ይልቅ፣ እግዚአብሔር አስተሳሰባቸውን እንዲለውጥ እጠይቀዋለሁ።

*ሦስተኛ*፣ ስለ ሕይወቴ ያለኝን ራእይ እንደገና በመገምገም፣ እግዚአብሔር ከቤተ ክርስቲያኒቱ አሳብ ጋር የሚጣጣም ራእይ እንዲሰጠኝ ልጠይቀው እችላለሁ። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ጊዜያዊ አገልግሎቶችን ከሰጠኝ በኋላ የኋላ ኋላ የሕይወት ጥሪዬ ይፈጸማል። ወንጌላውያን ለመሆን ተጠርተው ሳለ መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ጥሪያቸውን ያልተቀበለችላቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በግብርና ወይም በሌሎች ሥራዎች ላይ ይቆያሉ። እግዚአብሔር የመሪዎቹን ልብ በሚለውጥበት ጊዜ ግን መሪዎቹ በደስታ ወንጌላውያን አድርገው ይልኳቸዋል።

*አራተኛ*፣ በጸጥታ ያችን ቤተ ክርስቲያን ለቅቄ በመውጣት እግዚአብሔር በልቤ ውስጥ ካስቀመጠው ራእይ ጋር የሚመሳሰል አገልግሎት ወዳላት ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ።

በጉልበት ሽማግሌዎችን ገፍቶ የራስን ራእይ ተግባራዊ ማድረጉ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። በሌላ በኩል፣ አንዳንድ ጊዜ በአንድ ስፍራ ያለ ራእይ እያገለገሉ ለረዥም ጊዜ መቆየቱም እግዚአብሔር የሚፈልገው ነገር አይደለም። እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀው ራእይ አካል ያልሆነ ተግባር እየፈጸሙ መኖሩ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዳንሰጥና ለብስጭት እንድንዳረግ ሊያደርገን ይችላል። እግዚአብሔር እንድናከናውን በሰጠን ጉዳይ ከመሳተፍ በላይ የአገልግሎት ደስታን የሚያመጣ ምንም የለም። እግዚአብሔ

ር እንድታከናውን ሸክም በሰጣት ጉዳይ ላይ ከመሥራት በላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስደስት ምንም የለም።

> 3ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሕይወትህን ለመምራት የምትፈልግበት መንገድ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችሁን ከሚመራበት ሁኔታ ጋር የሚስማማው ወይም የማይስማማው እንዴት እንደ ሆነ አብራራ። ለ) አንዳንድ ጊዜ ባለህበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር የሰጠህን ራእይ ሳይፈጸሙ ከመኖር ይልቅ ከራእይህ ጋር የሚመሳሰል አገልግሎት ወዳላት ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው? ሐ) ራእያቸው እኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማየት ከምንፈልገው ነገር ጋር በሚለይበት ጊዜ ከሽማግሌዎች ጋር በመጣላት የሰይጣን መሣሪያ መሆን የሌለብን ለምንድን ነው?

4. *«ዕቅዴን በወረቀት ላይ ጽፌአለሁ። እግዚአብሔር ዕቅዴን እንደሚደግፍና እንደሚረዳኝ የሚያረጋግጡልኝን ጥቅሶች ከዕቅዱ አጠገብ ጽፌአሁ። ከዚህ ውጭ ሌላ ማድረግ ያለብኝ ነገር የለም።»* ብዙውን ጊዜ ራእይ በወረቀት ላይ የምናሰፍረው ነገር እንደ ሆነ በማሰብ ተግባራዊ ሳናደርገው እንቀራለን። ዓመታዊ ዕቅዳችን ምን እንደ ሆነ የሚጠይቁ ቅጾች ከቀጣናው ወይም ከቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት ይላኩልናል። እኛም የተጠየቅነውን ባለማድረግ ላለማፈር ስንል ሰዎችን ያስደምማሉ የምንላቸውን አንዳንድ ነገሮች ጽፈን እናስረክባለን። እንደ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የጻፍነውን ነገር ስለምንወደው፣ በቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ላይ እንለጥፈዋለን። ነገር ግን የሚሆነው ነገር ይኸው ብቻ ነው። ዕቅዶቹ ላይ የሚሠራ ሰው አይመደብም። ዕቅድ ወረቀት ሳይሆን፣ አንድ ቦታ ለመድረስ የምንጓዝበት መንገድ ነው። በጎዳናው ላይ እስካልሄድን ድረስ፣ ጎዳናው የሚሰጠን ጥቅም የለውም። በተመሳሳይ መንገድ፣ ዕቅዱን ተግባራዊ እስካላደረግን፣ ምንም ጥቅም የለውም። እንዲያውም፣ በግድግዳ ላይ የምንሰቅለው ወረቀት ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ቃል ኪዳን ያደረግንበት ነው። እግዚአብሔር ውሸት መናገርን ወይም የገቡትን ቃል አለመፈጸምን እንደሚጠላ ሁሉ፣ ዕቅዶችን ጽፈን ከፍጻሜ ላይ ለማድረግ ምንም ዓይነት ጥረት ሳናደርግ ስንቀር ደስ አይለውም። ተግባራዊ የማናደርጋቸውን



ዕቅዶች ከማውጣት ይልቅ መጀመሪያውኑ ዕቅድ አለማውጣቱ የተሻለ ነው።

*5. «ዕቅድ ማውጣት ስሕተት ነው። እግዚአብሔር በያዕቆብ 4:13-16 ላይ ዕቅድ ማውጣት ስሕተት ነው ብሎ የለ? መንፈስ ቅዱስ የሚነግረንን ሰምተን ዛሬ ማድረግ ያለብንን ነገር ማድረግ ብቻ ነው ያለብን። እርሱ ዕለት በዕለት ይመራናል።»* ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ዕቅድን እንደሚያከብር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል። እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ያቅድና ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉትን እርምጃዎች ይወስዳል። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በመስቀል ላይ እንደሚሞት ዐቅዷል። ይህንንም ያደረገው ድርጊቱ ከመፈጸሙ በሺዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ነበር (1ኛ ጴጥ. 1:19-20)። በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥ ለመጨረሻው ዘመን የወጠነውን ዕቅድ ገልጾልናል። እርሱ ለእኔና ለአንተ ዕቅድ አለው። ይህም እኛን መጥራትን፣ ለማዳን መወሰንን፣ ማዳንንና ማክበርን የሚያካትት ነው (ሮሜ 8:28-30)። እግዚአብሔር ዕለት በዕለት ከእኛ ጋር በመመላለስ ዕለታዊ ፍላጎታችንን ብቻ አያሟላም። እርሱ ወደ ላቀው ፍጻሜ ይወስደናል። መጽሐፈ ምሳሌ ሰዎች በጥበብ ዕቅዶችን እንዲያወጡ ያበረታታል። ምሳሌ 24:3-4 እንደሚያስተምረን፣ አንድ ነገር በጥሩ ሁኔታ የሚሠራው በጥሩ ሁኔታ የታቀደ እንደ ሆነ ነው። ጳውሎስ በመልእክቶቹ ውስጥ ስለ ዕቅዶቹ ይናገራል። ለምሳሌ፣ ለሮሜ አማኞች መጀመሪያ ወደ ሮም የመሄድና ከዚያ በኋላ ወደ ስፔን የመሄድ ዕቅድ እንዳለው ነግሯቸዋል (ሮሜ 15:23-29)። ይህም እግዚአብሔር ማቀድን እንደማይቃወም ያሳየናል።

ያዕቆብ የጻፈው ያለ እግዚአብሔር ኑሯችንን ልንወስን እንደምንችልና በራሳችን ጥበብ ሁሉንም ነገር ልናደርግ እንችላለን የሚለውን የትዕቢት አስተሳሰብ በመቃወም ነው። ለዚህ ነው ያዕቆብ አመለካከታችን፣ «እግዚአብሔር ቢፈቅድ» የሚል መሆን አለበት የሚለን። አማኞች እንደ መሆናችን፣ ዕቅዶቻችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ ማስገዛት አለብን። እግዚአብሔር ታላቅ ዓላማውን ለማሳካት ዕቅዶቻችንን የመቆጣጠርና የመለወጥ

መብት እንዳለው ማመን አለብን:: ስለሆነም፣ ጳውሎስ ስለ ዕቅዶቹ በሚናገርበት ጊዜ፣ «እግዚአብሔር ቢፈቅድ» ይላል:: (የሐዋ. 18:21፣ 1ኛ ቆሮ. 4:19ን አንብብ::) ማቀድ አስተዋይነት ከመሆኑም በላይ፣ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ነገር ነው:: ነገር ግን ዕቅዶቻችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛታችንንና እርሱ መንግሥቱን ለማስፋፋት እንዲጠቀምበት መጠየቃችንን ማረጋገጥ አለብን:: ሁልጊዜም መንፈስ ቅዱስ ዕቅዶቻችንን እንድንቀይር የሚጠይቀን ከሆነ፣ ይህንኑ ለማድረግ ዝግጁዎች መሆን አለብን:: ይህም ሆኖ ማቀድ አለብን:: መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ዕቅዳችንን በመንደፉ ረገድም ሆነ በመለወጡ በኩል ሊረዳን ይችላል::

ማቀድ መሪ የመሆን አስፈላጊ አካል ሲሆን፣ እግዚአብሔርንም የሚያስከብር ነገር ነው:: ሰዎችን ወደ ዕድገትና ለውጥ የሚመራ ዕቅድ ከሌለን፣ ራእይ ያለው አመራር እየሰጠን አይደለም ማለት ነው:: የአስተዳደር ሥራ ብቻ በመሥራት ላይ ነን ማለት ነው:: ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ማድረግ ከፈለግክ፣ በዓለም ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ከወደድክ፣ ጥሩ ዕቅድ የማውጣትን ክህሎት መማር ይኖርብሃል:: አንድ መሪ ለእግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን እንዲያደርግ የሚያስችለው ደረጃ በደረጃ ወደ ግብ ለመድረስ የሚያስችለው ዕቅድ ነው:: የኤሊና የጥንቸል ታሪክ እንደሚያስተምረን (ኤሊና ጥንቸል . . . ሁለቱ ሩጫ እየተወዳደሩ ሳለ ጥንቸል በጣም ሮጣ ትቀድምና ኤሊ እስክትደርስባት ታርፋለች:: ኤሊ ግን ሳታቋርጥ ቀስ እያለች በመሄድ ሩጫውን ታሸንፋለች)፣ ቀስ በቀስና ዳሩ ግን ባለማቋረጥ ወደ ግባቸው የሚጓዙ ሰዎች ሁልጊዜም ያሸንፋሉ:: ዕቅድ የሌላቸው ወይም ግባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ባለማቋረጥ የማይሠሩ ሰዎች ብዙም ፍሬያማ አይሆኑም:: ለእግዚአብሔር አንድ ታላቅ ተግባር ለማከናወን ትፈልጋለህ? እንግዲያውስ ዕቅድ ማውጣትን ተማር:: ቤተ ክርስቲያናችሁ በማኅበረሰቡ ውስጥ ለውጥ እንድታመጣ ትፈልጋለህ? ጥሩ ዕቅድ የማውጣት ክህሎትን ተማር::



4ኛ ጥያቄ፡- በቤተ ክርስቲያናችሁ ኮንፍረንስ ልታካሂዱ ነው እንበል:: ሀ) እግዚአብሔርን በማያስከብር ደካማ ዕቅድና እግዚአብሔርን በሚያስከብር ጥሩ ዕቅድ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ:: ለ) በእነዚህ ሁለት ዕቅዶች መካከል ያለው የአመለካከት ልዩነት ምንድን ነው?

## ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት የሚያስችሉትን ደረጃዎች ለማመልከት የምንጠቀምባቸውን ቃላት መረዳት

ይህ ትምህርት ግልጽ እንዲሆን ከተፈለገ፣ ጥሩ ዕቅዶችን ለማውጣት የምንጠቀምባቸውን ቃላት መረዳት አለብን:: በዚህ ክፍል የምንጠቀምባቸው ሦስት ዐበይት ቃላት እሉ፡-

1. ራእይ ወይም ንዑስ-ራእይ፡- ይህ ዕቅዶቻችንን ተግባራዊ አድርገን ስናበቃ ስለምናገኘው ውጤት ያለን ግንዛቤ ነው:: ለምሳሌ ያህል፣ ራእያችን «በሳል ቤተ ክርስቲያን መመሥረት»፣ ወይም ንዑስ ራእያችን፣ «እያንዳንዱ ምእመን በትጋት ለማያምኑ ሰዎች ከመመስከሩም በላይ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ቦታዎች ወንጌላውያንን ለመላክ እንዲቻል ገንዘብ ይሰጣል» የሚል ሊሆን ይችላል::

2. ውስን ግብ፡- ውሱን ግብ ራእያችንን ለመፈጸም የምናከናውነው ዋንኛ እርምጃ ነው:: ለምሳሌ፣ አማኞች ለክርስቶስ እንዲመሰክሩ ማስቻል የሚለውን ንዑስ ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ የምንጠቀምበት ውስን ግብ፣ «በሳምንት አንድ ቀን የምስክርነት ተግባር የሚፈጽሙ 6 የምስክርነት ቡድኖችን መመሥረት» ሊሆን ይችላል:: «አማኞች ሁሉ ለማያምኑ ሰዎች እንዴት እምነታቸውን እንደሚያካፍሉ ይማራሉ፣» የሚሉ ዓይነት ሌሎችም ውስን ግቦች ሊኖሩ ይችላሉ:: ውስን ግብ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ራእይ ለማድረስ የምታከናውነው ተግባር ነው:: (ማስታወሻ፡- የሥራ አመራር መጻሕፍት ብዙውን ጊዜ እነዚህን ውስን ግቦች «ዓላማዎች» በማለት ይጠሯቸዋል::)

3. ዝርዝር ተግባራት፡- እነዚህ ውስን ግቦችን እውን ለማድረግ የምናከናውናቸው ተግባራት ናቸው:: ስለሆነም፣ ውስን ግባችን ስድስት የምስክርነት ቡድኖችን መመሥረት ከሆነ፣ ዝርዝሩ ተ

ግባር፣ «የምስክርነት ቡድን አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆኑ አባላትን መጠየቅ» የሚል ሊሆን ይችላል። እንደምትመለከተው፣ ዝርዝር ተግባር ከግባችን ለመድረስ የሚያግዘን አንድ ተግባር ነው።

## በጥሩ ሁኔታ የታቀደ አገልግሎት ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ እውን እንድታደርግና በአገልግሎቷ ፍሬያማና ውጤታማ እንድትሆን፣ በሚገባ የታሰበበት ዕቅድ መውጣት አለበት። ማንኛውም ዕቅድ እግዚአብሔርን የሚያስከብርና ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን እንድትፈጽም የሚረዳት፣ ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉትን የዕቅድ ደረጃዎች ከተከተለች ነው።

1. ደረጃ አንድ፡- ጥሩ ዕቅድ የሚጀምረው ለማከናወን ስለምንፈልገው ተግባር ግልጽ ራእይና እግዚአብሔርን የሚያስከብር **ዓላማ** ከመወሰን ነው። ራእዩ ትልቅ ከሆነ (ለምሳሌ፣ በሳል ቤተ ክርስቲያን)፣ በንዑሳን ራእዮች መከፋፈል አለበት። እነዚህ ንዑሳን ራእዮች ትልቁን ራእይ እውን የሚያደርጉ ናቸው።

2. ደረጃ ሁለት፡- ግልጽ ዕቅድ እግዚአብሔር በሰጠን ራእይ ላይ በምንሠራበት ጊዜ ለመፈጸም የምንፈልጋቸውን ውስን ግቦች ይዘረዝራል።

3. ደረጃ ሦስት፡- ውስን ግቦቻችን እውን እንዲሆኑ መከናወን ያለባቸውን **ዝርዝር** ተግባ**ራት** መዘርዘር አለብን። በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ ወዘተ. . . መፈጸም ያለባቸው ነገሮች ተገቢ ቦታቸውን እንዲይዙ ዝርዝር ተግባራት በቅደም-ተከተል **መ**ደርደር አለባቸው።

4. ደረጃ አራት፡- እያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር መቼ እንደሚፈጸም የሚያሳይ የ**ጊዜ ሰሌዳ** አውጣ። እሁኑኑ፣ ከአንድ **ወር** በኋላ፣ ከአንድ ዓመት በኋላ፣ ወዘተ. . . የሚፈጸሙ ነገሮች ተለይተው **መቀመጥ** አለባቸው።



5. ደረጃ አምስት- ዕቅዱን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የሰው ኃይልና ሀብት ዘርዝር። ማን ምን ይሠራል? ዕቅዱን ለመፈጸም ለእያንዳንዱ ተግባር ስንት ብር ያስፈልጋል?

6. ደረጃ ስድስት- የዕቅዱን አፈጻጸም ከጊዜ ወደ ጊዜ መገምገም ያስፈልጋል። ይህ ራእዩን እውን ወደ ማድረጉ አቅጣጫ በመጓዝ ላይ መሆናችንን ያሳያል። እንዲሁም ደግሞ ዕቅዶቻችንን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ማስተካከያ የምናደርግበትን ዕድል ይሰጠናል።

በአመዛኙ ጥሩ ዕቅድ የምናወጣው፣ «ለምን፣ እንዴት፣ ምን፣ የት፣ መቼ፣ እና ማን?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ነው። ያቀድነውን ተግባር የምናከናውነው *ለምንድን ነው?* ራእዩ ወይም ዕቅዱ እውን እንዲሆን መፈጸም ያለበት ነገር *ምንድን ነው?* ለማድረግ የምንፈልገውን ነገር የምናከናውነው *እንዴት* ነው? ተግባራዊ ለማድረግ የምንፈልገውን ነገር የምናከናውነው *የት* ነው? *መቼ* ነው የምናደርገው? *ማን* ነው የሚያደርገው? እነዚህን ጥያቄዎች አንሥተን የምናገኘው መልስ በዕቅድ ሂደታችን ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ይመራናል።

(ማስታወሻ፡- ይህ ጥሩ ዕቅድ የማዘጋጀቱ ሂደት ለትልቅ ራእይም ሆነ [ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ወደ መንፈሳዊ ብስለት መምራት እንደሚቻል]፣ ለትንሽ ራእይ [ለምሳሌ፣ ኮንፍረንስ ማዘጋጀት] የሚሠራ ነው። ለግል ራእይ [ለምሳሌ፣ ዩኒቨርስቲ መግባት] ወይም ዕቅድም እንዲሁ ይሠራል። ማስታወስ ያለብህ፣ እየተነጋገርን ያለነው እመራራችንን ስለሚያሳድግ ክህሎት መሆኑን ነው። እነዚህ ደረጃዎች በመጀመሪያ አስቸጋሪዎች ቢመስሉም፣ ክህሎቱን ከተማርክ በኋላ ቀላል በመሆናቸው፣ መሪዎች በቀላሉ እነዚህን ደረጃዎች ተጠቅመው ጥሩ ዕቅድ ሊያወጡ ይችላሉ። የአገልግሎትህን የትኛውንም ክፍል በምታቅድበት ጊዜ እነዚህን ደረጃዎች መጠቀም ጀምር። በእነዚህ ደረጃዎች እገዛ በምታዘጋጀው ጥሩ ዕቅድና ለእግዚአብሔር ክብር በምታከናውነው ተግባር ትደነቃለህ። በመጨረሻም ዕቅድ ማውጣት ልማድህ ይሆናል።)

5ኛ ጥያቄ፡- አሁኑኑ ጊዜ ወስደህ እነዚህን ስድስት የዕቅድ ደረጃዎች ክለስ፡፡

## ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት የሚያግዙ ደረጃዎች

እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ እውን ማድረግ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ ራእዩን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል የሚያሳይ ዕቅድ ማውጣት ነው፡፡ በአብዛኛው መሪዎች እንዲከሰቱ የሚፈልጓቸውን ነገሮች (ራእያቸውን) በመጻፍ ብዙ ይደከማሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን በጽሑፍ ስላሰፈሩ ብቻ እውን የሚሆን ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን ራእይ ስላለን ብቻ ጠብ የሚል ነገር አይኖርም፡፡ ግልጽ ዕቅዶች የማውጣቱን ጠቃሚ ሁለተኛ እርምጃ ካልወሰድን፣ ራእይ ማዘጋጀታችን ጊዜ ከማባከን ያለፈ አይሆንም፡፡ እግዚአብሔር ራእይን የሚሰጠን ራእዩን ተግባራዊ ለማድረግ እንድናቅድ ነው፡፡ መጀመሪያ ዕቅዶቻችንን በማጥራት ብዙ ጊዜ ከወሰድን፣ የተሻሉ አገልግሎቶችን ልናዘጋጅ እንችላለን፡፡ መሪዎች ወደ ራእዩ የሚደረገውን ጉዞ እየተከታተሉ የተለያዩ ኃላፊነቶችን ለሌሎች ሰዎች በውክልና ለመስጠት ይቀልላቸዋል፡፡

***ደረጃ አንድ፡- ለማከናወን ስለምንፈልገው ተግባር ግልጽ ራእይና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ዓላማ መወሰን፡፡*** (ማስታወሻ፡- እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ራእይ ለመረዳት ትምህርት ስምንትንና ዘጠኝን ክለስ፡፡ ይህ በዕቅድ ውስጥ የመጀመሪያውና እጅግ አስፈላጊው እርምጃ ነው፡፡)

ለእግዚአብሔር ምን ለማከናወን እንደምንፈልግ ካላወቅን፣ ራእዩን ለመፈጸም ዝርዝር ዕቅዶች ማውጣት እንደማይቻል ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ በሳልና እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ማኅበረ ምእመናን የሚቀይር ዕቅድ ለማውጣት የመጀመሪያው እርምጃ በጸሎትና በጥንቃቄ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ራእይ መወሰን ነው፡፡ ማቀድ ከመጀመራችን በፊት ምን ለማከናወን እንደምንፈልግ በግልጽ መረዳት አለብን፡፡ ይህ በቤተ ክርስቲያን የአንድ ቀን ሥራ እንደ ማከናወን ያሉትን የአጭር ጊዜ አገልግሎቶች ወይም የረዥም ጊዜ አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ እማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚያግዝ የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ማዘጋጀትን) የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ ራእዮቹን እውን ለማድረግ ዕቅዶቻችንን ከማውጣታችን በፊት ሊከናወን የተፈለገው ነገር በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡ የትኛውም ራእይ እግዚአብሔርን እንዲያስከብር ከተፈለገ፣ መሪዎች ከራስ-ወዳድነት ዓላማዎቻቸው ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት በሚፈልጉ ምክንያቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡

[ማስታወሻ፡- ራእዩ አነስተኛ (ለምሳሌ፣ ኮንፍረንስ ማካሄድ) ከሆነ፣ ምናልባትም ራእዩን በንዑስን ራእዮች መከፋፈል አያስፈልግም ይሆናል፡፡ ነገር ግን፣ ወደ ቀጣዩ ደረጃ በመሸጋገር፣ ኮንፍረንሱ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማስቻል ዕቅዶችን ልናወጣ እንችላለን፡፡]

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ራእይ በጣም ሰፊ በመሆኑ ምክንያት ግልጽ ዕቅዶችን ለማውጣት የሚያዳግት ከሆነ፣ መሪዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለባቸው፡-

*1. ራእዩ ትልቅ ከሆነ፣ በንዑሳን ክፍሎች መከፋፈል አለብን፡፡* አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ዐበይት ራእዮች በጣም ሰፋፊ በመሆናቸው፣ ጥሩ ዕቅዶች ማውጣቱ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ራእዩ እውን እንዲሆን ሊያግዙ በሚችሉ ዐበይት የአገልግሎት ክፍሎች መከፋፈል ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ፣ በሳል ቤተ ክርስቲያን የመፍጠር ዐቢይ ራእይ ቢኖረን፣ በሚከተሉት ክፍሎች ልንከፋፍለው እንችላለን፡- 1) የወንጌል ስርጭት፣ 2) ማስተማር፣ 3) መሪዎችን ማሳደግ፣ 4) አምልኮ፣ 5) ለድሆች ክርስቲያናዊ ፍቅር ማሳየት፣ ወዘተ. . .

ዐቢዩን ራእይ በምድቦች መከፋፈሉ በእያንዳንዱ አገልግሎት ላይ በግል ደረጃ እንድናተኩር ያስችለናል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የተለያዩ አገልግሎቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መካሄዳቸውንና በአንደኛው የራእያችን ክፍል (ለምሳሌ፣ የወንጌል ስርጭት) ላይ እየሠራን፣ ሌላውን የራእያችንን ክፍል (ለምሳሌ፣ አማኞችን ወደ መንፈሳዊ ብስለት ማድረስ) ቸል አለማለታችንን እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ የቤተ

ክርስቲያን አገልግሎቶች «ሚዛናዊ» በሆነ መንገድ መካሄዳቸው እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፡፡ በወንጌል ስርጭት ንዑስ ራእይ ጠንካራ ሆና ሳለ፣ በማስተማር ንዑስ ራእይ የተዳከመች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እያስከበረች አይደለም፡፡ ምክንያቱም ምእመናኗ በሳል መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብዙም ሳይቆይ ሰይጣን ሐሰተኛ ትምህርቶችን ተጠቅሞ ችግሮችን መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡ እግዚአብሔርን የምናስከብር ቤተ ክርስቲያን ለመሆን፣ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች ሚዛናዊነትን በጠበቀ መንገድ መካሄድ አለባቸው፡፡

2. እያንዳንዱ ዋና ንዑስ ራእይ የየራሱ የ«ራእይ መግለጫ» ወይም ግብ ያስፈልገዋል፡፡ ይህ መግለጫ እግዚአብሔር ያንን አገልግሎት ክባረከ ምን ውጤት ማየት እንደምንፈልግ የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ክበሳል ቤተ ክርስቲያን ዋና ዋና ንዑሳን ራእዮች አንዱ የወንጌል ስርጭት ነው፡፡ ስለዚህ የወንጌል ስርጭት ራእያችን፣ *«እያንዳንዱ አማኝ ለማያምኑ ሰዎች መመስከር መቻሉና ወንጌላውያንን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመላክ በልግስና ገንዘብ መስጠቱ»* ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ራእይ በወንጌል ስርጭት ንዑስ ራእይ ላይ ትኩረት እንድናደርግና የተግባር ዕቅዶችን እንድናወጣ ያስችለናል፡፡ መሪዎች በእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በመመልከት ወደ ራእዩ የሚደረገውን ግስጋሴ እንዲገመግሙ ያስችላቸዋል፡፡

6ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ አንድ ሰፊ ራእይ ምረጥ፡፡ ለ) ሰፊውን ራእይ በንዑሳን ራእዮች ከፋፍል፡፡ ሐ) ለእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ እግዚአብሔር እንዲከናወን ይፈልጋል የምትለውን የራእይ መግለጫ ጻፍ፡፡ «እግዚአብሔር ቢፈቅድ፣ ራእያችን . . . » እያልክ ጻፍ፡፡ የምትጽፈው እግዚአብሔር እንዲፈጽም የምትፈልገውን ተግባር ሳይሆን፣ ራእዩ በሚፈጸምበት ጊዜ ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ግብ መሆኑን እትዘንጋ፡፡

**(ማስታወሻ፡- በቀጣይ ጥያቄዎች ውስጥ ዕቅዶችን ለማውጣት ይህንን ራእይ ስለምትጠቀምበት፣ ንዑስ ራእዮችህን ጊዜ ወስደህ በጥሩ ሁኔታ ጻፍ፡፡ በሳምንታዊ ስብሰባውም ላይ አንዳንድ አሳቦችህን ታካፍላለህ፡፡)**



**ደረጃ ሁለት፡- እግዚአብሔር በሰጠን ራእይ ላይ በምንሠራበት ጊዜ ለመፈጸም የምንፈልጋቸውን ውስን ግቦች መዘርዘር፡፡**

ከአመራር እጅግ አስፈላጊ ተግባራት አንዱ ግልጽና አጠቃላይ የሆነ ዕቅድ ማውጣት ነው፡፡ ግልጽ ያልሆነ ራእይ አገልግሎታችን ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ ግልጽ ራእይ ግን መሪዎች ብዙ ጥረትና ገንዘብ ሳያባክኑ ክፍተኛ ተግባራት እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል፡፡ መሪዎች በዚህ ዕቅድ የማውጣት ሥራ ላይ ብዙ ጊዜ ባጠፉ ቁጥር፣ ሥራው በሚጀመርበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ያድናሉ፡፡

[ማስታወሻ፡- አንዳንድ ጊዜ ለወደፊት ከማቀዳችን በፊት፣ ያለፈውን መለስ ብለን መገምገም ይኖርብናል፡፡ አንድ ሐኪም ለበሽተኛ መድኃኒት ከማዘዙ በፊት፣ መጀመሪያ የተከሰተውን ችግር መርምሮ ከውሳኔ ላይ ይደርሳል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት ካላካሄደች፣ ወይም አማኞች በመንፈሳዊ ብስለት እያደጉ ካልሆነ፣ ወይም ለማኅበረሰቡ ፍቅር ካላሳዩ፣ መሪዎች እነዚህ አገልግሎቶች ለምን እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንደማይካሄዱ ማጥናት አለባቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ደካማ የሆነችበትን ምክንያት ካወቁ በኋላ፣ እነዚህን ድክመቶች ለማስተካከል የሚያስችሉ ጥሩ ዕ ቅዶች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡]

ትልቁ ራእያችንን በንዑሳን ራእዮች ከከፋፈልን በኋላ፣ ስእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ዕቅዶችን ማውጣት አለብን፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ በሁለት ደረጃዎች የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ <u>በመጀመሪያ</u>፣ ንዑስ ራእዩን በውስን ግቦች መክፋፈል አለብን፡፡ እነዚህ ውስን ግቦች ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ ራእዩ እውን ይሆናል ማለት ነው፡፡ <u>ሁለተኛ</u>፣ ለእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ግቡን ለመምታት የሚያስችሉትን ተግባራት እንዘረዝራለን፡፡ ብዙውን ጊዜ ውስን ግቦች ራእዩን ለመፈጸም ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

ማከናወን የምንፈልጋቸውን ተግባራት ከመዘርዘራችን በፊት፣ ራእዩን (ንዑስ ራእዩን) በውስን ግቦች መክፋፈል አለብን፡፡ እነዚህ

ውስን ግቦች በሚጠናቀቁበት ጊዜ፣ ራእዩ እውን ይሆናል:: እነዚህ ውስን ግቦች ራእዩን ለማሳካት መከናወን ያለባቸው ሥራዎች ናቸው:: እነዚህን ምድቦች በግልጽ ከዘረዘርን፣ እነዚህን ክፍፍሎች ለአገልግሎቱ ወደሚጠቅም ጥሩ የተግባር ዕቅድ መቀየሩ ቀላል ነው:: ለምሳሌ፣ ራእያችን ኮንፍረንስ ማዘጋጀት ከሆነ፣ ራእዩን በሚከተሉት ነገሮች ልንከፋፍለው እንችሳለን:- 1) በወንጌል ስርጭት ላይ የሚናገር ታዋቂ ሰባኪና ኳየር መጋበዝ፣ 2) ለ100 ሰ ዎች ምግብና መኝታ ማዘጋጀት፣ 3) ለ3000 ሰዎች ዳስ መሥራት፣ 4) በቀበሌያችን ውስጥ የሚገኙ የወንጌሳውያን አብያተ ክርስቲያናት አባሳት በኮንፈረንሱ እንዲሳተፉ መጋበዝ::

ራእያችን «እያንዳንዱ ምእመን ሰማያምኑ ሰዎች በትጋት በመመስከርና ወንጌሳውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ይሳኩ ዘንድ ገንዘቡን በልግስና ይሰጣል» የሚል ከሆነ፣ የሚከተሉትን ዓይነት ነገሮች መዘርዘር ይቻሳል:-

ሀ. እያንዳንዱ አማኝ የወንጌሉን መልእክት ጥርት አድርጎ ስለሚረዳ፣ የራሉን መዳንና ሌሎችም ይድኑ ዘንድ ምን ዓይነት መልእክት ሊያካፍሳቸው እንደሚገባ ያውቃል::

ለ. እያንዳንዱ አማኝ እምነቱን ሌሳ ሃይማኖት ለሚከተሉ ሰ ዎች እንዴት እንደሚያካፍል ያውቃል::

ሐ. እያንዳንዱ አማኝ እምነቱን ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ሰማያምኑ ሰዎች ያካፍሳል::

መ. የማኅበረሰቡ አባሳት ወንጌል የመስማት ዕድል እንዲኖራቸው ቤተ ክርስቲያን ከምእመኖቿ ግማሾቹን እምነታቸውን ለማኅበረሰቡ አባላት እንዲያካፍሉ ታደርጋለች::

ሠ. ምእመናን ሁሉ ለወንጌል ስርጭት የሚሰጡትን ገንዘብ በ50 በመቶ ይጨምራሉ::

ረ. ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የኢትዮጵያ ክፍሎች 5 ወንጌሳውያንን አሠልጥናና ደመወዛቸውን ከፍላ ትልካቸዋለች::



እያንዳንዱ ምእመን በወንጌል ስርጭት ላይ ጠንካራ ተሳትፎ እንዲያደርግና ቤተ ክርስቲያንም በአጠቃሳይ በራእዩ ውስጥ እንደተ መለከተው ሳልዳኑት ሰዎች ወንጌልን እንድታደርስ መከናወን ካለባቸው ነገሮች እንዳንዶቹ ከሳይ የተመለከቱት ናቸው::

| |
|---|
| 7ኛ ጥያቄ:- ሀ) ራእዩን እውን ለማድረግ በዚህ የወንጌል ስርጭት ሥራ ላይ ሊጨመሩ የሚችሉ አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ባለፈው ሳምንት ያጠናነውን «የአምልኮ» ክፍል ተግባራዊ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን ልትጠቀም የምትችላቸውን አምስት ነገሮች ዘርዝር:: |

## ሁለት ዓይነት ውስን ግቦች

1. መፈጸም አለመፈጸማቸውን ለማረጋገጥ መለካት የምንችሳቸው አንዳንድ ውስን ግቦች አሉ:: አንዳንድ አስተዳዳሪዎች ውስን ግቦቻቸውን የሚገልጹት መለካት በሚቻልበት መንገድ ነው:: ይህ አንድ ለው አልሞ ለመምታት እንደሚያነጣጥርበት «ዒሳማ»፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ እውን ለማድረግ በመንቀሳቀስ ሳይ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: በመሆኑም፣ ማኅበ ረሰቡን በወንጌል እንደርሳለን ከማለት ይልቅ፣ ይበልጥ ውስን ሆነው በየሳምንቱ ለማኅበረሰቡ ወንጌልን የሚመሰክሩ አምስት የምስክርነት ቡድኖች እንደሚያቋቁሙ ይናገራሉ:: እንዲህ ዓይነት ሊለኩ የሚችሉ ግቦች ማስፈር ውስን ግቦቻችንን ለመገምገም ከማስቻሉም በሳይ፣ አንዳች ነገር እያከናወንን መሆናችንን ለማወቅ ያግዛል::

2. ስለዚህ፣ እንድ ነገር መፈጸማችንን ለመለካት ከመሞከር ይልቅ ውስጣዊ ለውጥንና መንፈሳዊ ዕድገትን የሚጠቁሙ ነገሮችን መፈለግ አለብን:: ከሥራችን በሳይ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ልባችንና ከልባችን የሚመነጩ ምክንያቶች ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ወደ እንድ አቅጣጫ እየተ ጓዝን መሆናችንን በሚያሳዩ ሊለኩ የሚችሉ ውጫዊ ነገሮች ላይ ብቻ መወሰን የለብንም:: ለዎች ውስጣዊ ዕድገት እያሳዩ መሆናቸውን በሚያመለከቱ የባሕርይና የልባዊ ፍሳጎት ለውጦችም ሳይ ትኩረት ማድረግ አለብን:: በለዎች ልብና ባሕርይ ላይ ትኩ

ረት ካላደረግን፣ ሊጨበጡ የሚችሉ ግቦች የማስናከያ ዓለቶች ሊሆኑብን ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ወንጌሉን በጥሩ ሁኔታ ባለማቅ ረባቸው ወይም መስካሪዎቹ ከሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት እንሻላለን የሚል ባሕርይ በማሳየታቸው ምክንያት ማኅበረሰቡ እንዲጠላን የሚያደርጉ አምስት የምስክርነት ቡድኖችን ብንልክ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን ራእያችን እውን አልሆነም። ሰይጣን «የምስክርነት ቡድን» አባላትን ወይም ወንጌላውያንን በመጠቀም ትዕቢትን ሊፈጥር ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ እግዚአብሔርን እንደማያስደስትና የምስክርነት ማኅበረሰብ የመሆን ራእያችንን እንደማያለካው ግልጽ ነው። ያልዳኑትን፣ በተለይም የሚጠሉህን የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች፣ መውደድን እንዴት ትለካዋለህ? አንድ ሰው እንዳለው፣ «በሕይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች የማይለኩ ናቸው።» በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ለማምጣት የምንፈልጋቸው እጅግ አስፈላጊ ለውጦች በሰዎች ልብ ውስጥ የተ ደበቁ በመሆናቸው፣ ለመለካት ቀላል አይደሉም።

| |
|---|
| 8ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሊለኩ የሚችሉ ሦስት ውስን ግቦችን ጻፍ። ለ) በቀላሉ ሊለኩ የማይችሉ ሦስት ግቦችን ጻፍ። ሐ) መንፈሳዊ ብስለትን የበለጠ የሚገልጸው የትኛው ዓይነት ግብ ይመስልሃል? |

## ውስን ግቦችን ለመጻፍ የሚያግዝ ምክር

በችሎታ የተካኑ የሥራ አስተዳዳሪዎች (ቢዝነስ ማናጀሮች) ጥሩ ዕቅዶችን ለማውጣት የሚያስችሉ ውስን ግቦችን ለመጻፍ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይገባል ሲሉ ይመክራሉ፦

*1. ውስን ግቦቹ አጠቃላይ መሆን አለባቸው።* ግቡን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነው ተግባር በሙሉ መገለጽ አለበት። ከላይ ስለ ወንጌል ስርጭት የተጠቀምንበት ምሳሌ እንደሚያሳየው፣ ይህ አማኞች ማድረግና ማወቅ ያለባቸውን ሁሉ ያካትታል። ቤተ ክርስቲያን ማድረግ ያለባትንም ነገር እንዲሁ ይጨምራል። ዕቅዱ አጠቃላይና ሚዛናዊ የሚሆነው ራእዩን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮች በሙሉ ከተዳሰሱ በኋላ ነው።



*2. ውስን ግቦች ሕዝቡ የሚሠራበትን ግብ በሚያመለክት መንገድ መገለጽ አለባቸው።* ግብ ግልጽ ስለሆነ ብዙውን ጊዜ ስንፈጽመው እናውቀዋለን። እነዚህ ግቦች ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን ወደ መፈጸሙ አቅጣጫ እየተጓዘች ነው የሚል ምልክት ያሳያሉ። ለምሳሌ፣ በወንጌል ስርጭት ላይ አንደኛው ክፍል ግቡ «እያንዳንዱ አማኝ እምነቱን በሳምንት ሁለት ጊዜ ለማያምን ሰው ያካፍላል!» ይላል። እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች መልሶ ይገነባ ዘንድ የነህምያን ልብ ባነሣሣ ጊዜ፣ ነህምያ ዕቅድ አውጥቶ ነበር። ያ ዕ ቅድ ዝም ብሎ ደብዛዛ «ተስፋ» አልነበረም። ሊለኩ የሚችሉ ነገሮች ነበሩት። በመሆኑም፣ ንጉሡ ሥራው ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅበት በጠየቀው ጊዜ፣ ነህምያ ግልጽ ምላሽ ለመስጠት ችሎ ነበር (ነህ. 2:4)። ብዙውን ጊዜ ውስን ግቦች ውጤታማ የማይሆኑት አንድ ተጨባጭ ነገር ለመሥራት ወደሚያስችል አቅጣጫ የምንቀሳቀስበትን ሁነኛ ነገር ስለማይሰጡን ነው። ለምሳሌ፣ ለቤተ ክርስቲያናችን ካሉን ግቦች አንዱ «ለወንጌል አገልግሎት ሰዎች ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሰጡ ማድረግ» ነው የሚል ሊሆን ይችላል። ይህ ጥሩ ግብ ነው። ነገር ግን ግቡ ተ ግባራዊ መሆኑ የሚታወቀው እንዴት ነው? የሚበቃው ተጨማሪ ገንዘብ ምን ያህል ነው? የአምስት ብር ጭማሪ ብቻ ያረካናል? ጥርት ብሎ የማይታይ ግብ በሥራችን የምንገፋበትን ነገር ስለ ማያስጨብጠን፣ ራእያችንን ለመጨበጥ አያስችለንም። ነገር ግን የተወሰነ ቁጥር፣ ለምሳሌ በዓመት 1000 ብር ከሰጠን፣ በትክክል የምንፈልገው ነገር እየተከናወነ መሆኑን እንረዳለን።

ስለዚህ ውስን ግቦችን በጸሎት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ «በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ምእመኖቻችን ለወንጌል የሚሰጡትን ገንዘብ በ20 በመቶ ለመጨመር እንፈልጋለን፣» ልንል እንችላለን። ይህ ማለት ሁለት ዓመታት ሲጠናቀቁ፣ ግባችንን መምታት አለመምታታችንን እናውቃለን ማለት ነው። ካልሆነ፣ ግቡን ለመምታት ማሻሻል ያለብን ነገር ካለ ዘወር ብለን እንመ ረምራለን ማለት ነው። ግልጽ ግብ ማዘጋጀት በጸሎታችን ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለብንም ያሳየናል። «ብዙ እንድንለግ እርዳን!» ከማለት ይልቅ፣ አሁን፣ «ጌታ ሆይ፣ ቢያንስ 20

በመቶ ተጨማሪ በመስጠት እንድናስከብርህ እርዳን፣» ብለን ልንጸልይ እንችላለን። ግልጽ ግብ ሕዝቡ ግልጽ ተግባር እንዲያከናውኑም ይረዳል። ቤተ ክርስቲያን ለወንጌላውያን ስለሚሰጥ ገንዘብ ሠንጠረዥ አዘጋጅታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፊት ለፊት በሚታይ ስፍራ ብታስቀምጥ፣ እያንዳንዱ ምእመን እግዚአብሔር እንዴት እየሠራና እየባረካቸው እንደ ሆነ ይረዳል። እግዚአብሔር ሰዎች ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሰጡ ለማነሣሣት እንዲህ ዓይነቱን ሠንጠረዥ ይጠቀማል።

*3. ውስን ግቦች ራእዩን እንዴት እውን እንደሚያደርጉ ማሳየት አለባቸው።* ዝርዝሩ ግብ በግልጽ ወደ ራእዩ የማይወስደን ከሆነ፣ ራእዩ እንዴት እየተፈጸመ እንዳለ ለማሳየት ለማከናወን የምንሞክረውን ነገር መቀየር አለብን፣ ወይም ግቡን በዚህ ራእይ ውስጥ ማካተት የለብንም። ምናልባትም ሌላ ራእይ ለመፈጸም የሚረዳ ሌላ ምድብ ማዘጋጀት ሊኖርብን ይችላል። ለምሳሌ፣ «አዲስ ቤተ ክርስቲያን መገንባት፣» የሚለውን ተግባር ከወንጌል ስርጭት ንዑስ ራእይ ሥር ብናስገባ፣ ይህ እንዴት የወንጌል ስርጭትን እንደሚረዳ ማወቅ አይቻልም። ነገር ግን «ለአዳዲስ አማኞች ቦታ ለማግኘትና ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን መጥተው እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዲፈልጉ ለማነሣሣት አዲስ ሕንጻ እንገነባለን» ቢባል፣ ይህ ዐቢይ ተግባር እንዴት ለወንጌል ስርጭት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መመልከት ይቻላል። ግቡ የቤተ ክርስቲያን ሕንጸ መገንባት አይደለም፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻውን በመጠቀም የወንጌል ስርጭትን ማጠናከር እንጂ። ሕንጻው ያልዳኑትን ሰዎች ለመድረስ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ የሚያስችል መሣሪያ እንጂ ግብ አይደለም።

ከላይ ስለ ወንጌል ስርጭት ከቀረበው ማብራሪያ እንደምትመለከተው፣ ውስን ግቦች ወደ ራእያችን እየተጓዝን መሆናችንን ወይም አለመሆናችንን በሚገባ ያሳያሉ። ግልጽ ካልሆኑ ግን፣ መከናወን አለመከናወናቸውን ለማወቅ ያስቸግራል። ስለዚህ፣ ውስን ግቦች ወደ ራእያችን እየሄድን መሆን አለመሆናችንን ለመረዳትና ለመገምገም የሚያግዙን መሆን አለባቸው።



*4. እነዚህ ውሱን ግቦች «እምነትን» ይጠይቃሉ።* አሁን እየተከናወኑ ያሉትን ነገሮች በወረቀት ላይ አስፍሮ ግባችን ይኼ ነው ማለቱ ዋጋ የለውም። ለምሳሌ፣ «ባለፈው ዓመት 300 ብር ስለ ሰጠን ዘንድሮም 300 ብር እንሰጣለን» ማለት በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣትንና ለማደግ አለመፈለግን ያሳያል። ለማደግ ከፈለግን፣ እንድንለወጥና እግዚአብሔር ከሚፈልገው ደረጃ እንድንደርስ የሚያግዙንን ግቦች ማሰብ አለብን።

*5. ውሱን ግቦች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆን አለባቸው።* ግቦቹ ከቤተ ክርስቲያን አቅም በላይ ያለፉ «ተስፋዎች» ወይም «ሕልሞች» ብቻ ከሆኑ፣ ሕዝቡ ተስፋ ስለሚቆርጡ ለመሞከር እንኳን ላይደፍሩ ይችላሉ። አንድ መሪ ለትንሽ ቤተ ክርስቲያን፣ «2000 ሰዎች መያዝ የሚችል ሕንጻ እንሥራ» ቢል፣ ሕዝቡ ሕልሙን ሊሆን እንደማይችል ስለሚያስቡ ምንም ዓይነት ተግባራዊ እርምጃ ላይወስዱ ይችላሉ። ለአብዛኞቹ ነገሮች፣ ግባችን መሆን ያለበት ሰዎች የበለጠ እንዲሠሩ የሚያነሣሣቸውና ሕዝቡ በእግዚአብሔር ርዳታ ልንወጣው እንችላለን ብለው የሚያስቡት መሆን አለበት።

*6. ውሱን ግቦቹ እግዚአብሔር በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣት ራእይ ጋር መጣጣም አለባቸው።* ሕዝቡ ይህ የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ ወደፊት የሚያራምድ እንጂ፣ መሪዎች ደስ ስላላቸው ብቻ የሚያደርጉት አለመሆኑን መረዳት አለባቸው። ሕዝቡ ለወንጌል ስርጭት አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንጸ መገንባት የሚያስፈልግበትን ምክንያት ካላወቁ፣ ለአዲስ ሕንጻ ግንባታ ራሳቸውን በመሥዋዕትነት ላይሰጡ ይችላሉ።

*7. ውሱን ግቦች ቤተ ክርስቲያን የምታከናውናቸው የአጭር ጊዜ ተግባራት በአንድ ጊዜ እንዲቀየሩ ማድረግ የለባቸውም።* እግዚአብሔር በፍጹም የተለየ ነገር እንዲያደርጉ በግልጽ ካልተናገራቸው በስተቀር፣ ውስን ግቦቹ ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ስታደርግ ከነበረችው ነገር ጋር መመሳሰል አለባቸው። ዐበይት ለውጦች መምጣት ያለባቸው ቀስ በቀስ ሊሆን ይገባል። በአጠቃላይ፣ ሰዎች ለውጥን ስለማይወዱ፣ ነገሮች በፍጥነት

በሚለወጡበት ጊዜ ይቃወማሉ። ስለሆነም፣ ዐበይት ግቦችንና ዕቅዶችን በምናስተዋውቅበት ጊዜ ለውጦቹ መምጣት ያለባቸው ቀስ በቀስ በዓመታት ውስጥ መሆን አለበት። ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት ገንዘብ የምትሰጠው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበረ እንበል። ነገር ግን መሪዎች እያንዳንዱ አማኝ በቀጥታ ገንዘቡን ለወንጌላዊው እንዲሰጥ ቢወስኑ፣ ይህ የምእመናንን ተቃውሞና ግራ መጋባት ሊያስከትል ይችላል። ይህም ለወንጌል ስርጭት የሚሰጠው ገንዘብ እስከናካቴው እንዲቆም ሊያደርግ ይችላል።

*8. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሌሎች አገልግሎቶችን ውስን ግቦች ሚዛናዊነት መጠበቅ አለባቸው።* ለወንጌል ስርጭት ውስን ግቦችን የሚነድፍ አንድ ቡድን፣ «ከመባዎቻችን 90 በመቶውን የምንሰጠው ለብሔራዊ ወንጌላውያን ነው» ቢል፣ ምእመናንን የማስተማር ውስን ግቦችን የሚያዘጋጀው ቡድን በምን ገንዘብ ነው ሥራውን ማካሄድ ያለበት? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት አጠቃቀም በማመጣጠን ሁሉም ዐበይት አገልግሎቶች አብረው እንዲያድጉ ማድረግ አለባቸው። ይህ አንዱ አገልግሎት እያደገ ሌሎች ደካሞች ሆነው እንዳይቀሩ ያደርጋል። ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ሚዛናዊ የሆነ አገልግሎት ታካሂዳለች። ውስን ግቦቻችንም ይህንኑ ማንጸባረቅ አለባቸው።

ይህ አሳብ ግራ የሚያጋባና አስቸጋሪ ነውን? የግልጽ ዕቅድ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ደረጃዎች ለመመለስ የሚሞክሩት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ነው፤ በመጀመሪያ፣ «ምን ለማድረግ እየሞከርን ነው?» እና <u>ሁለተኛ</u>፣ «ግቦቻችንን ተግባራዊ ለማድረግ ልናከናውናቸው የሚገቡን ዓበይት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?» ኮንፍረንስ ለማዘጋጀት ብትፈልጉ፣ መጀመሪያ መነሣት ያለበት ጥያቄ፣ «በኮንፍረንሱ አማካኝነት ማከናወን የምንፈልገው ተግባር ምንድን ነው?» የሚል መሆን አለበት። ይህ ከተወሰነ በኋላ፣ ሁለተኛው ጥያቄ፣ ማለትም፣ «በዚህ ኮንፍረንስ ለማከናወን የምንፈልገው ተግባር እውን እንዲሆንልን ምን ምን ነገሮችን ማድረግ አለብን» የሚለው ይከተላል።



[ማስታወሻ:- ይህ ባለ ሁለት ደረጃ ሂደት ለግል ራእዮችም ይሠራል። «ለእግዚአብሔር ክብር በሕይወቴ ምን ለማድረግ እፈልጋለሁ?» ብለን ብንጠይቅና መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ በመሥራት ወንጌላዊ ሆነን ወንጌል ላልደረሰባቸው የገጠር ቦታዎች እንድናገለግል ቢቀሰቅሰን (ይህ ራእይን ከእግዚአብሔር ዘንድ ማግኘት የመጀመሪያው ደረጃ ነው)፣ መጠየቅ ያለብን ቀጣዩ ጥያቄ፣ «ወንጌላዊ ለመሆን ምን ምን ደረጃዎችን ማለፍ አለብኝ?» የሚል ይሆናል። በዚህ ጊዜ የሚከተሉትን ዓይነት ነገሮች መዘርዘር ይቻላል፣ ሀ) በቂ መደበኛ ትምህርት ማግኘት፣ ለ) በቂ የሥነ-መለኮት ትምህርት ማግኘት፣ ሐ) እምነቴን ለማካፈል የሚረዳ ባህል-ዘለል ሥልጠና መውሰድ፣ መ) ሌሎች ሃይማኖቶች ለሚከተሉ ሰዎች እምነታችንን የማካፈል ልምድ ማካበት፣ ሠ) አገልግሎቴን በገንዘብና በጸሎት እንዲደግፉ ከመሪዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ ወዘተ. . . (ይህ ውስን ግቦችን መመሥረት የሚባለው ሁለተኛው ደረጃ ነው።)

ይህ ምን እንደሚያደርግ አጢን። ወዲያውኑ እግዚአብሔር የሰጠንን ግብ ለመምታት የሚያስፈልጉንን ነገሮች እናውቃለን። በቂ የቀለም ትምህርት ከሌለን፣ ከመጀመሪያው ጀምረን ትምህርታችንን እንከታተላለን። ከዚያም ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት እንከታተላለን። በዚህ ጊዜ ትኩረት ማድረግ ያለብን ሌላ እምነት ለሚከተሉ ሰዎች እምነታችንን እንዴት ማካፈል እንዳለብን ይሆናል። ምናልባትም ከረምት ከረምት ትምህርት ቤት ሲዘጋ ልምድ ካላቸው ወንጌላውያን ጋር እየተገናኘን እምነታችንን ለሌሎች እንዴት እንደምናካፍል ልምድ እንቀስማለን። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወንጌላዊ የመሆን ፍላጎት እንዳለን እንነግራቸውና ማኅበረሰቡን በወንጌል የመድረስ ራእያቸውን ለማሟላት አብረናቸው እንሠራለን። ራእዩን እውን ለማድረግ እነዚህን ሁሉ ውስን ግቦች በማከናወን እግዚአብሔር ብቃት ያለን ወንጌላዊ እንድንሆን የሰጠንን ራእይ ተግባራዊ እናደርጋለን።]

> ፱ ጥያቄ:- ሀ) ለሕይወትህ ያለህን የግል ራእይ ጻፍ። ለ) ራእዩ እውን እንዲሆን ልትወስዳቸው የሚገቡህን ደረጃዎች ዘርዝር።

**ከላይ የቀረቡትን ሁለት ደረጃዎች መፈጸሙ ራሱ ለቤተ ክርስቲያን ዕቅዶችን በክህሎት የመገንባት እርምጃችንን ራቅ አድርጎ ይወስደዋል:: ለማከናወን ለምትፈልጓቸው ነገሮች ሁሉ እነዚህን ሁለት ነገሮች ብትጠቀሙ፣ ዕቅድ የማውጣት ችሎታችሁ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል::**

| |
|---|
| 10ኛ ጥያቄ:- በጥያቄ 6 ላይ ያዘጋጀኸውን የራእይ መግለጫ በመጠቀም፣ ራእዩ እንዴት እውን እንደሚሆን የሚያሳዩ ቢያንስ አምስት ውስን ግቦችን ጻፍ:: እነዚህን ግቦች ለመጻፍ ከላይ የቀረቡትን መመሪያዎች ተጠቀም:: በተቻለ መጠን አጠቃላይ ተግባራትን ለማሳየት ሞክር:: |

## ሁለተኛ ቀን

እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም የሚጠቀምባቸውን ጥሩ ዕቅዶች ስለ ማዘጋጀት እያጠናን ነው:: ዕቅድ ማውጣት ሦስት ዐበይት ደረጃዎችን እንደሚያካትት ተመልክተናል:: ደረጃ አንድ - አገልግሎታችንን በምንፈጽምበት ጊዜ ምን ለማየት እንደምንፈልግ በግልጽ መረዳት ነው:: ይህንን «ራእይ» ብለን ጠርተናል:: ደረጃ ሁለት- እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም የሚያግዙ ውስን ግቦችን ማዘጋጀት ነው:: ደረጃ ሦስት- ዛሬ የምናጠናውና የጻፍናቸውን ውስን ግቦች ለመፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራት ናቸው::

**ደረጃ ሦስት:-** ውስን ግቦቻችን እውን እንዲሆኑ መከናወን ያለባቸውን ዝርዝር ተግባራት መዘርዘር::

*1. አንድን ውስን ግብ እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ዝርዝር ተግባራት በሙሉ አስፍር::* በደረጃ ሁለት ውስጥ የገለጽናቸው እያንዳንዳቸው ውስን ግቦች ከአሳብ ደረጃ ወደ እውነታ ይቀየሩ ዘንድ ብዙ ተግባራት መከናወን አለባቸው:: እነዚህ ዝርዝር ተግባራት «እንዴት» ነው ከግባችን የምንደርሰው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጡናል:: በደረጃ አንድ ራእዩ እውን እንዲሆን የሚያስፈልጉትን ነገሮች የዘረዘርን ሲሆን፣ አሁን የምንዘረዝረው ለውስን ግቦች መተግበር አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት ነው::



ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስርጭት ራእይዋን እንድታሰፋ በሚያስችለው ምሳሌያችን ውስጥ ከተጠቀሱት ውስን ግቦች አንዱ፣ *«እያንዳንዱ አማኝ ወንጌሉን በግልጽ በመረዳት መዳኑንና ሌሎች እንዲድኑ የሚያካፍለውን መልእክት ያውቃል፣»* የሚል ነበር:: እሁን ለዚህ ግብ መፈጸም መከናወን ያለባቸውን ዝርዝር ተግባራት እንዘረዝራለን:: የሚከተሉትን ዓይነት ነገሮች በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሊሰፍሩ ይችላሉ:-

ሀ. የምእመናንን ዝርዝር ከቤተ ክርስቲያን መዝገብ በመመልከት አባሎቻችን እነማን እንደ ሆኑ ማወቅ::

ለ. ለሥልጠና ፕሮግራም ቀን መወሰን::

ሐ. ለምእመናን የምናስተምራቸውን ነገሮች መዘርዘር::

መ. ለምእመናን እነዚህን ርእስ-ጉዳዮች የሚያስተምር ሰው መምረጥ::

ሠ. እያንዳንዱ ምእመን ወደ ሥልጠናው ፕሮግራም መምጣቱን ማረጋገጥ::

*2. ዝርዝር ተግባራቱን በሚከናወኑበት ቅደም ተከተል አስፍር::* ብዙውን ጊዜ ዕቅድ በምናወጣበት ወቅት የተወሰኑ ነገሮች ከሌሎች ቀድመው መከናወን አለባቸው:: ስለሆነም፣ ዕቅዳችን በድርጊቶች ቅደም-ተከተል መሠረት መደራጀት አለበት:: ለምሳሌ ያህል፣ በወንጌል ስርጭት ምሳሌያችን ውስጥ ምእመናን በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዲመሰክሩ ከመላካቸው በፊት ስለ ወንጌሉና ስለ ምስክርነት ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል:: ቅደም-ተከተሉ ከተዛባ፣ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ:: ወንጌሉን የማያውቁ ሰዎችን ለምስክርነት ብንልካቸው፣ ለማያምኑ ሰዎች የሚናገሩት ነገር ትክክል ላይሆን ይችላል:: ወንጌልን የሚመሰክሩ እየመሰላቸው የማያምኑ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መጀመሪያ አኗኗራቸውን መለወጥ እንደሚያስፈልጋቸው የሚናገሩ ሰዎች አሉ:: ይህ መዳን በመልካም ሥራ ይገኛል የሚል ሐሰተኛ ወንጌል ነው:: ሌላ ሃይማኖት ካላቸው ሰዎች ጋር እንዴት በጥንቃቄ መነጋገር እንዳለባቸው ከማወቃቸው በፊት ከላክናቸው፣

ብዙ አላስፈላጊ ተቃውሞ በወንጌሉ ላይ ሊመጣ ይችላል:: ስለሆነም፣ ግባችንን የሚመቱ ነገሮችን በትክክለኛው ቅደም ተከተላቸው ማደራጀት አለብን::

> 11ኛ ጥያቄ:- በጥያቄ 10 ላይ ከጻፍካቸው ውስን ግቦች ለሁለቱ ዝርዝር ተግባራት ጻፍ:: ዝርዝር ተግባራቱ ውስን ግቦቹን ከፍጻሜ የሚያደርሱ መሆናቸውን አትዘንጋ:: እያንዳንዱ ተግባር በክንውን ቅደም ተከተል ጻፍ::

*3. አገልግሎቱን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች በዝርዝር ዕቅዱ ዝግጅት ተካፋይ መሆን አለባቸው::* በኋላ ስለ ውክልና ስንማር (ፍቺውን ከታች ተመልከት) ብዙውን ጊዜ እነዚህ ዝርዝር ተግባራት በሽማግሌዎች እንደማይዘጋጁ እንመለከታለን:: ሽማግሌዎች ሌሎች ሰዎች አጠቃላይ የሆነ ዕቅድ እንዲያወጡ ይጠይቃሉ:: ግቦቹን እውን በማድረጉ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች በዚህ ደረጃ ላይ መሳተፋቸው ወሳኝ ነው:: አንድ ሰው በዚህ የሂደቱ ክፍል ውስጥ ካልተሳተፈ፣ ብዙውን ጊዜ ተግባራቱን ለማከናወን ተግቶ ላይሠራ ይችላል:: ቤት ተከራይ የባለቤቱን ያህል ለቤቱ እንክብካቤ እንደማያደርግ ሁሉ፣ የዕቅዱ አካል ያልነበሩ ሰዎች በዕቅዱ ውስጥ የተሳተፉትን ያህል ሙሉ የአገልግሎቱ ተሳታፊዎች አይሆኑም:: ስለሆነም፣ በማቀዱ ሥራ ላይ መሳተፍ ያለባቸው ተግባራዊውን ሥራ የሚያከናውኑ ሰዎች ጭምር እንጂ፣ ሽማግሌዎች ብቻ መሆን የለባቸውም::

*4. የሌላ ሰውን ዕቅዶች ላለመቅዳት ተጠንቀቅ::* ለቤተ ክርስቲያናችሁ ሁኔታ እንደሚመች አድርገህ ልታዘጋጀው ትችላለህ:: የሌላውን ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን ሥራዎች መኮረጅ የለብንም:: ነገር ግን፣ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሥራዎቿን እንደምታከናውን ካወቅን በኋላ፣ ነገሮችን የምንሻሽልባቸውንና ከራሳችን ዓውድ ጋር የምናስማማባቸውን መንገዶች መፈለግ አለብን:: ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የሚያደርጓቸው ብዙ ነገሮች በተለይም ከፍተኛ የባሕል ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ (ለምሳሌ፣ የምዕራቡ ዓለም) ለእኛ ሁኔታ ላይሠሩ ይችላሉ:: ጥሩ አሳቦች ከእኛ ዐውድ (ሁኔታ) ጋር እንዲስማሙ መደረግ ያስፈልጋቸዋል::



> 12ኛ ጥያቄ:- በሌላ ቤተ ክርስቲያን እና ባሕል ውስጥ የሠራ አንድ ተግባር በቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም በባሕላችሁ ላይሠራ ሲቀር ያየህበትን ምሳሌ ጥቀስ::

**ደረጃ አራት:- እያንዳንዱ ዝርዝር ተግባር መቼ እንደሚፈጸም የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ አውጣ::**

አንድን ግብ ለመምታት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት በሙሉ ከዘረዘርን በኋላ፣ እያንዳንዱ ተግባር መቼ እንዲከናወን እንደምንፈልግ በጸሎት «ቀን» መወሰኑ ተገቢ ነው:: «እግዚአብሔር ቢፈቅድ፣ በዚህ ጊዜ እንዲህና እንዲህ እናደርጋለን::» ይህ ተግባሩ «መቼ» ይፈጸማል? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል::

ለምሳሌ፣ በሳል ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የወንጌል ስርጭት የማካሄዱን ንዑስ ራእይ በመውሰድ፣ በጳጉሜ ውስጥ ዓመታዊ ዕቅድ እያወጣን ብንሆን፣ በመስከረም 15 እያንዳንዱ አማኝ የወንጌልን ምንነት የሚረዳበትን ሥልጠና እንሰጠዋለን ልንል እንችላለን:: ጥቅምት 15፣ ምእመናኑ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ለሆኑት ሰዎች እንዴት እምነታቸውን እንደሚያካፍሉ እናስተምራቸዋለን:: በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ፣ እግዚአብሔር የወንጌላዊነት ስጦታ የሰጣቸውና የጠራቸው ሁለት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ተመርጠው ለሥልጠና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ:: በአምስት ዓመታት ውስጥ የእነዚህን ወንጌላውያን ደመወዝ ችለን በኢትዮጵያ ውስጥ በወንጌላዊነት እንዲሠሩ እንልካቸዋለን::

ለነገሮች ጊዜ በምንወስንበት ጊዜ፣ ይህንን የምናደርገው የዕድገትን ፍጥነት የሚወስነው እግዚአብሔር መሆኑን ባለመዘንጋት ነው:: ለቆረጥናቸው ቀናት ራሳችንን ባሮች በማድረግ፣ ነገሮች በፈለግነው ፍጥነት በማይሄዱበት ጊዜ አልተሳካልንም ከሚል ፍርሐት ውስጥ እንወድቅም:: ከቁጥጥራችን ውጭ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ:: የእግዚአብሔርን መንፈስ ቀድመን ልንሄድ አንችልም:: በሌላ በኩል፣ እነዚህን የጊዜ ገደቦች እንደ ዋዛ እንመለከታቸውም:: እነዚህ «በእምነት ለእግዚአብሔር የገባናቸው

ቃል ኪዳኖች» ናቸው፡፡ «ጌታ ሆይ፣ በምንችለው ሁሉ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይህንን እንሠራለን» ማለታችን ነው፡፡

ሥራችንን ለማጠናቀቅ የጊዜ ሰሌዳ ማውጣቱ ዕድገት እያሳየን መሆናችንን ለማወቅ ያግዘናል፡፡ እንዲሁም ደግሞ «በሚቀጥለው ወር እንሠራዋለን» እያሉ ከወር እስከ ወር ምንም ሳይሠሩ የመኖርን ተፈጥሯዊ የመዘግየት ዝንባሌ ያስወግዳል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ራሳችንን እንድንገመግምም ያግዘናል፡፡ ተግባራዊ ይሆናል ብለን በጸሎት ያወጣነውን የጊዜ ሰሌዳ ካልጠበቅን፣ «ለምን አልሠራሁትም?» ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን፡፡ ሰነፎች ሆነን ሥራችንን ስላላከናወንን ነው? ምእመናን የጠበቅነውን ያህል በፍጥነት ለሥራው ዝግጁዎች ባለመሆናቸው ነው? ምእመናንን በግድ የማይፈልጉትን ሥራ ልናሠራቸው እንደማንችል ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ምእመናንን ከመጫን ይልቅ፣ እግዚአብሔር ልባቸውን እንዲያዘጋጅ መጸለይ አለብን፡፡ ወይስ የዘገየው ከቁጥጥራችን ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ነው? ለምሳሌ ያህል፣ የመምህሩ መታመምና ለመምጣት አለመቻል? እንፈጽማለን ብለን የወጠንናቸውን ግቦች ለምን እንዳልፈጸምን ካወቅን በኋላ፣ ሌላ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ግባችንን ለመምታት እንሞክራለን፡፡

| |
|---|
| 13ኛ ጥያቄ፡- ውስን ግቦቹ እንዲከናወኑ መፈጸም አለባቸው ብለህ ያወጣሃቸውን ዝርዝር ተግባራት ተመልከህ እይ፡፡ ከእያንዳንዱ ተግባር አጠገብ፣ መቼ መፈጸም እንዳለበት የሚያሳይ ቀን ጻፍ፡፡ |

**ደረጃ አምስት፡- ዕቅዱን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የሰው ኃይልና ሀብት ዘርዝር፡፡**

ምን ማድረግ እንደምንፈልግና መቼ እንደምናከናውን ካወቅን በኋላ፣ ዝርዝር ተግባራቱን ለማሳካት ምን ዓይነት ሀብት እንደሚያስፈልጉ ልንዘረዝር እንችላለን፡፡ ሀብት ስንል ስለ ሁለት ዐበይት ነገሮች መናገራችን ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ሰዎች መናገራችን ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ገንዘብ ወይም ቁሳዊ ነገሮች መናገራችን ነው፡፡

**1. እያንዳንዱን ዝርዝር ተግባር ማን እንደሚያከናውን ጻፍ፡፡**



ሰዎች እግዚአብሔር ራእዩን እውን ለማድረግ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ትልቅ ሀብት ናቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሥራ የሚሠራው በሰዎች ነው፡፡ ለዚህ ነው ኢየሱስ በሥራ በደከመ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁልጊዜም ዝግጁና የነጣ የአገልግሎት መስክ እንደሚጠብቃቸው በመረዳት ምእመናን እግዚአብሔር ተጨማሪ «ሠራተኞችን» እንዲሰጥ እንዲለምኑ የነገራቸው፡፡ (ሉቃስ 10፡1-2ን እንብብ፡፡) እግዚአብሔር ሰው እንዲሰጠን እንጂ ገንዘብ እንዲሰጠን ጸልዩ አላለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ እውን ለማድረግ ሕዝቦቿ ከምንም በላይ ትልቅ ሀብት መሆናቸውን ካልተገነዘበች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ለውጥ ሊኖር አይችልም፡፡ ሽማግሌዎች ሁሉንም ሥራ ለማከናወን ይሞክሩና ይሳናቸዋል፡፡ በዚህም ተናድደው አገልግሎታቸውን ይተዉታል፡፡ ምእመናን እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚጠብቀው እሑድ እሑድ መጥተው በወንበሮች ላይ እንዲቀመጡ እንጂ እግዚአብሔር በሚያከናውነው ወይም ሊያከናውን በሚፈልገው ነገር ውስጥ እንዲሳተፉ መሆኑን ሳያውቁ ይችላሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱ አማኝ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግልና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ ለመፈጸም ትችል ዘንድ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ መንፈሳዊ ስጦታ ሰጥቶታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናንን በማነቃነቅ እንደ መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸው ለመጠቀም ካልቻሉ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኖቻችን ያሰበውን ራእይ ልንፈጽም አንችልም፡፡

ከዚህ በታች የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሀብት የሆኑትን ምእመናን ለመጠቀም የሚያስችሉ እውነቶች ተመልከተዋል፡-

*ሀ. በዕቅዳችን ውስጥ ላሰፈርናቸው ለእያንዳንዳቸው ዝርዝር ተግባራት እነዚያኑ ተግባራት የሚያከናውን አንድ ሰው እንመድባለን፡፡ ይህ የዕቅድ ደረጃ «ማን» የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፡፡ አንዳንድ ተግባራት የሚከናወኑት እንደ ሽማግሌዎች ስብሰብ ባለ ቡድን ሊሆን ይችላል፡፡ አብዛኞቹ ተግባራት የሚከናወኑት ግን በግለሰቦች ነው፡፡ ተግባራት የሚከናወኑት «አባት» ሲኖራቸው ነው፡፡ ኃላፊነት የሚወስድ ሰው ያልተ*

ስየመሳቸው ተግባራት ሳይፈጸሙ ሊቀሩ ይችላሉ:: ዕቅዱ ከጸደቀ በኋላ ተግባራቱን የማከናወን ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ምን ማድረግና መቼ ማከናወን እንዳለባቸው ሊነገራቸው ይገባል:: መሪዎች የዕቅዱን ዕድገት በሚከታተሉበት ጊዜ፣ ለእያንዳንዱ የዕቅድ አካል ማን ኃላፊነት እንዳለበት ማወቅ አለባቸው:: በዚህ መንገድ ሰዎች በኃላፊነት የወሰዱትን የዕቅድ አካል የመፈጸም ተጠያቂነት እንዳለባቸው ልናሳውቅ እንችላለን:: ብዙውን ጊዜ ዕቅዶች የማይጠናቀቁት ወይም በጥሩ ሁኔታ የማይጠናቀቁት ሥራውን ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች ስለማይኖሩ ነው:: መሪዎች ለምን አልሠራህም? የሚል ጥያቄ በሚያነሡበት ጊዜ፣ «የነገረኝ የለም» የሚል ምላሽ ይሰጣቸዋል::

ስለዚህ፣ እያንዳንዱን ተግባር በተመለከተ፣ «ይህን ተግባር ለማሳካት ምን ዓይነት ዕርዳታ ከማን እንፈልጋለን?» ብለን መጠየቅ አለብን:: እንበልና፣ ኮንፍረንስ ለማካሄድ ዕቅድ እያወጣን ነው:: ተናጋሪው ማን ይሆናል? ተናጋሪውን የሚጋብዘው ማን ነው? ለምግብ ማዘጋጃ የሚያስፈልጉትን ነገሮች የሚገዛው ማን ነው? ዳሱን የሚጥለውስ? የእንግዶችን መኝታ ስፍራ የሚያዘጋጀውስ ማን ነው? ወይም ደግሞ ምእመናን ለጎረቤቶቻቸው እንዲመሰክሩ ለማስቻል የሥልጠና ፕሮግራም እያካሄድን ከሆነ፣ «ማን ነው የሚያስተምረው? ሽማግሌዎችን የሚያስፈቅደው ማን ነው? ምእመናን ወደ ሥልጠናው እንዲመጡ ጥሪ የሚያደርገው ማን ነው? የምስክርነት ቡድኖቹን የሚመሩት እነማን ናቸው?» የሚሉ ጥያቄዎችን ልናነሣ እንችላለን::

በማይኖር ሰው ላይ የተመሠረተ ዕቅድ ማውጣቱ ዋጋ የለውም:: በመሆኑም፣ ተግባሮቻችሁን በምትዘረዝሩበት ጊዜ ከተግባሮቹ አንዱን የሚፈጽም ሰው ከሌለ፣ ለጊዜው ያንን ተግባር አለማቀዱ ይሻላል:: ነገር ግን፣ ወደፊት አንድ ሰው ሠልጥኖ የምትፈልጉትን ተግባር እንደሚያከናውን በግብነት ያዙት:: ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ሕጻናትን የማስተማር ሥልጠና የወሰደ ሰው ሳይኖር፣ በዚህ ዓመት የመዋዕለ ሕጻናት ትምህርት እንጀምራለን ማለቱ ጥሩ ዕቅድ አይሆንም:: ነገር ግን፣



ዕቅዳችሁን በማስተካከል አንድ ሰው ተመርጦ ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ ይኖርባችኋል:: ትምህርት ቤቱን መገንባትና ትምህርት መጀመር የሚያስፈልገው፣ የሠለጠነ ሰው ሲኖር ብቻ ነው::

*ለ. ራእይ ሊሳካ ወይም ላይሳካ የሚችለው ብዙውን ጊዜ ትክክለኛ ሰው ትክክለኛውን ሥራ እንዲያከናውን ከማድረግ ጋር በተያያዘ ነው::* ብዙውን ጊዜ አንድን ዕቅድ ለማሳካት ትልቁ ችግር ገንዘብ ማግኘት ሳይሆን ትክክለኛ ሰዎችን ማግኘት ነው:: ብዙ መሪዎች ትክክለኛ መዋቅር ካለን አገልግሎቱ ይጀመራል የሚል ስሕተት ይፈጽማሉ:: በዚህ እሳብ ተነሣሥተው ሕንጻውን ይሠራሉ:: ነገር ግን ሥራውን በሚጀምሩበት ጊዜ ፕሮግራሙ ግቡን እንዲመታ የሚያግዙ ሠራተኞች አይኖሯቸውም:: መጀመሪያ በሰዎች ላይ ትኩረት ማድረግን መማር አለብን:: ቤተ ክርስቲያን ራእይዋን እንድትፈጽም የሚያደርጉት፣ ሀ) ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ተመሳሳይ ራእይ ያላቸው፣ ለ) ትክክለኛውን ሥልጠና ያገኙ፣ ሐ) ቤተ ክርስቲያኒቱ መክፈል በምትችለው የገንዘብ መጠን ሥራውን የሚያከናውኑ ሰዎች ናቸው:: ትምህርት ቤት በጎጆ ቤት ውስጥ ሊጀመር ይችላል:: ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ውጤታማ የሚሆነው በቤቱ ማማር ሳይሆን፣ መምህሩ ጥሩ የማስተማር ችሎታ ያለው እንደ ሆነ ነው:: ጥራት ያላቸው ፕሮግራሞች የተገነቡት ጥራት ባላቸው ሰዎች ላይ እንጂ ውብ በሆኑ ሕንጻዎች ላይ አይደለም:: በዓለም ሁሉ መንግሥታት ግሩም ሕንጻዎችን ይሠራሉ:: ነገር ግን ፕሮግራሞቹን የሚያካሂዱ ሰዎች ጥራት ያለው ሥራ ስለማይሠሩ፣ መንግሥት የሚፈልገው ለውጥ እውን አይሆንም:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ተመሳሳይ ችግሮች ይፈጠራሉ::

*ሐ. ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም ምእመናን በማሠልጠን ለእግዚአብሔር ክብር የመሥራት ብቃታቸውን ማሳደግ አለባት::* ማን ነው ሥራ ያልበዛበት ማለት ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን የረዥም ጊዜ ዕቅድ በምናስብበት ጊዜ፣ «ሰዎች አገልግሎታቸውን በብቃት ይወጡ ዘንድ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?» የሚለውንም ጥያቄ ማንሣት አለብን:: የቤተ

ክርስቲያን ወሳኝ ሀብት ሕዝቦቿ ስለሆኑ፣ ሥራው የሚስፋፋው እነርሱ ሲያድጉ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ብቃት የሚወስነው ደግሞ ብዙውን ጊዜ የሰዎች የብቃት ማነስ ነው፡፡ ስለሆነም የእግዚአብሔርን ራእይ ተግባራዊ ለማድረግ የምትፈልግ ቤተ ክርስቲያን ምእመኖቿ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበትን ብቃት ለማሳደግ የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ አለባት፡፡ [ማስታወሻ:- ይህንን ትምህርት እግዚአብሔር ለሥራው «ሞኞችን» እና «ደካሞችን» እንደሚጠቀም ከሚያስረዳው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማመጣጠን አለብን (1ኛ ቆሮ. 1:26-29)፡፡ ትኩረት ማድ ረግ ያለብን እንደ ዓለማዊ ትምህርት «በመደበኛ» ትምህርት ላይ መሆን የለበትም፡፡ ይልቁንም፣ በመንፈሳዊ ባሕርያት፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችና እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎት በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱ ምእመን እግዚአብሔር እንዲጠቀምበት የሚፈልገው ብዙ ድብቅ ችሎታ እንዳለው፣ ዕድልና ሥልጠና ከሰጠናቸው፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መረዳት አለብን፡፡]

*መ. ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ሥራ የሚሰጥበትን አቅም ማሳደግ አለብን፡፡* በአመዛኙ የችግራችን ምንጭ የገንዘብ አለመኖር ይመስለናል፡፡ «ገንዘብ ቢኖረን ለእግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን እናደርግ ነበር» እንላለን፡፡ ለመሆኑ ገንዘብ የሚመጣው ከየት ነው? ገንዘብ የሚመጣው ከሕዝባችን ነው፡፡ የሰዎችን የመስጠት ፍላጎትና የሚሰጡበትን ምክንያት የሚገነዘቡበትን መንገድ ብናሳድግ፣ ገንዘብ መስጠታቸው የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም፣ አስተ ዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን እንደ የገንዘብ ምንጭ ወይም እንደ ጊዜያዊ ሠራተኞች ከመጠቀም ይልቅ፣ ሰዎችን በማ- ሳደጉ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ሰዎችን በምናሳድግበት ጊዜ፣ ብዙ ሰዎች ለአገልግሎት ራሳቸውን ይሰጣሉ፡፡ በአረኝነት ሽማግሌዎችን የሚያግዙ ብዙ ምእመናንም ይነሣሉ፡፡ ስለሆነም፣ የሰው ኃይልን



ማሳደግ እንደ አነስተኛ ጉዳይ የሚቆጠር ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው ነው፡፡

2. የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችሉትን የገንዘብና ቁሳዊ ሀብቶች መዘርዘር፡፡

አብዛኞቹ ዝርዝር ተግባራት የሆነ ዓይነት ቁሳዊ ወይም የገንዘብ ሀብት የሚጠይቁ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ገንዘብ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት አለብን፡፡ ሰዎችን የምናሠለጥን ከሆነ፣ ቤት ያስፈልገናል፡፡ ለአስተማሪው የትራንስፖርት አበል፣ ለኮንፍረንሱ ተሳታፊዎች የመኝታ ስፍራ፣ ለምግብ መሥሪያ የሚያስፈልጉ ነገሮች ያስፈልጉናል፡፡ ስለሆነም፣ ለእያንዳንዱ ተግባር የሚያስፈልጉትን ነገሮች መጻፍና እያንዳንዱ ነገር ስንት ብር እንደሚያወጣ መገመት አለብን፡፡ ለምእመኖቻችን የሥልጠና ፕሮግራም ለማካሄድ ስንት ብር ያስፈልገናል? ለተናጋሪ ው ትራንስፖርትና የስጦታ መግዣ ስንት ብር ያስፈልገናል? ለኮንፍረንሱ መጠለያ ለመሥራት ስንት ብር ይፈጃል? ለሥልጠና ቁሳቁሶች፣ ወንጌላውያንን ለመቅጠር ስንት ብር ያስፈልጋል? እነዚህ የገንዘብ ዕቅዶች ለዓመቱ በጀታችንን ለማዘጋጀት፣ እንዲሁም ምእመናን ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲሰጡ ለመጠየቅ የሚጠቅሙን ናቸው፡፡

በሉቃስ 14:28፣ 31 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር የትኛውንም ሥራ ከመጀመራችን በፊት ውጤቱንና የሚያስወጣውን ገንዘብ መተመን አስፈላጊ መሆኑን ገልጾአል፡፡ ገና ከመነሻው የጀመርነውን ነገር ማጠናቀቅ ስለ መቻላችን ማሰብ አለብን፡፡ ይህ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ለመሆን ብቻ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመር ለምትፈልጋቸው ዐበይት አገልግሎቶች ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ጊዜ ጥሩ አገልግሎት ይጀምሩና ወዲያውኑ የገንዘብ እጥረት ስለሚገጥማቸው አገልግሎቱ ይቆማል፡፡ ይህም ምእመናን መሪዎች የሚያመጧቸውን አዳዲስ የአገልግሎት አሳቦች በጥርጣሬ ዓይን እንዲያዩ ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ የገጠማቸው

ምእመናን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ራእይ ለመፈጸም አዳዲስ ነገሮች ለመጀመር ፈቃደኝት ሊያንሳቸው ይችላል።

ኢየሱስን በሚያስከብር መንገድ አንድን ተግባር ለመፈጸም ምን ያህል ገንዘብ እንደሚፈጅብን ካወቅን በኋላ ልናደርግ እንደምንችል ወይም እንደማንችል እናውቃለን። ወይም ደግሞ በቅናሽ ገንዘብ የሚካሄድበትን መንገድ እንፈልጋለን። ወይም ቤተ ክርስቲያን ተ የሚካሄድበትን መንገድ እንፈልጋለን። ወይም ቤተ ክርስቲያን ተ ግባሩን ለመሸፈን የሚያስችል ገንዘብ የምታገኝበትን መንገድ እናቅዳለን። ከምእመናን ገንዘብ የሚሰባሰብበትን ወይም አንዳንድ ለጋሾች ዕርዳታ የሚያደርጉበትን ሁኔታ እናመቻቻለን።

አንዳንድ ጊዜ «ዋጋ» ገንዘብ የሚያስወጣውን ነገር ብቻ ላያመለክት ይችላል። ተግባሩን ለመፈጸም የሚያስፈልግ የ«ጊዜ» ዋጋም አለ። ተግባሩ ከሽማግሌዎች ወይም ከሰብሳቢው ጊዜ ምን ያህል ይጠይቃል? ለዚህ ተግባር ጊዜ አላቸው? ካልሆነ፣ ሌላ ሰው መቅጠር ያስፈልግ ይሆን? ይኼስ ምን ያህል ገንዘብ ያስወጣናል? ከፍያውን ለመፈጸም በቂ ገንዘብ አለን?

ተግባሩን መፈጸም ወይም አለመፈጸም ስለሚያስከትለው «ትርፍና ኪሳራም» ማሰብ አለብን። ለማከናወን የምንሞክረው ነገር ባይሳካ፣ ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተ ጽዕኖ ምንድን ነው? (ለምሳሌ፣ ለመንግሥት የልማት ፕሮጀክት ለመሥራት ቃል ብንገባና ከአንድ ዓመት በኋላ ገንዘቡ ቢያልቅ?) ያቀድነውን ተግባር ብናከናውን፣ ይህ በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? (ለምሳሌ፣ የልማት ፕሮጀክት መጀመር ለመጋቢው ደመወዝ ከተ ያዘው በጀት እንድንወስድ ሊያስገድደን ይችላል። ያለ መጋቢ፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሊያድጉ አይችሉም። ይህ ካልሆነ ደግሞ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ትልቁ ዓላማ ሊሳካ አይችልም።)



የዕቅዱ ቅደም ተከተልም ትክክል መሆን አለበት። መጀመር ያለብን እግዚአብሔር እንድናደርግ ስለሚፈልገው ተግባር ዕቅድ በማዘጋጀት ነው። ከዚያ በኋላ የሚያስወጣው ገንዘብ ምን ያህል እንደ ሆነ መወሰን አለብን። ዕቅዳችን አሁን ባለን ገንዘብ ሊሸፈን የማይችል ከሆነ፣ ዕቅዱን በመከፋፈል የምንችለውን ያህል ማከናወን አለብን። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ በመመ ልከት በዚህ ገንዘብ ሊያከናውኑ የሚችሉትን ተግባር ያቅዳሉ። ቤተ ክርስቲያን 1000 ብር ካላት፣ «በዚህ ገንዘብ ምን እናድርግ?» ትላለች። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ገንዘብ አባካኞች መሆናችንን ያሳያል። ገንዘባችንን ዘለቄታዊ ጥቅም በማያስገኙና የእግዚአብሔ ርን መንግሥት ከሁሉም በላቀ ሁኔታ በማያስፋፉ ነገሮች ላይ እናጠፋለን። ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን ስሚለውጡና ራእይን ለሚፈጽሙ ነገሮች ማከናወኛ ገንዘብ አይኖረንም። እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብት በማስተዋል መጠቀም ካለብን፣ ለዕ ቅዱ እግዚአብሔርን ልንጠይቅና ያለንን ገንዘብ በመጠቀም ዕ ቅዱን ተግባራዊ ልናደርግ ይገባል።

> 14ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዕቅድህን ተግባራዊ በማድረግ ራእይህን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የገንዘብና የሰው ኃይል ዘርዝር። ለ) እነዚህን ደረጃዎች መከተልህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሻለ ዕቅድ ማውጣት እንዲቻል ምን ዓይነት ለውጦች ሊካሄዱ እንደሚገባ እንድትገነዘብ እንዴት እንደ ረዳህ ግለጽ። ሐ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች ለዐበይት ራእዮችም ሆነ ለአነስተኛ ጉዳዮች እነዚህን ደረጃዎች በመከተል ተግባሮቻቸውን ቢያከናውኑ ምን ዓይነት ለውጦቹ የሚካሄዱ ይመስልሃል?

## ጥሩ ዕቅዶች ለማውጣት የሚያግዙ ሁለት ሠንጠረዦች

የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንክ፣ የሚከተሉት ሠንጠረዦች እግዚአብሔር የሰጠህን ራእይ ለመፈጸም ጥሩ ዕቅዶችን እንድታወጣ ይረዱሃል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ካልሆንክ፣ ከሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር ከእነርሱ በምታገኘው መረጃ መሠ ረት ሠንጠረዥ አዘጋጅ። እነዚህን ሠንጠረዦች በምሳሌነት በመጠቀም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በትልቅ ወረቀት ላይ

ሠርተው እንደ ቤተ ክርስቲያናቸው ፍላጎት ሊያሟሏቸው ይችላሉ::

1. ሠንጠረዥ 1:- ራእዩን፣ ንዑሳን ራእዮችንና ውስን ግቦችን ዘርዝር:-

<table>
<tr><td colspan="3">የራእይ መግለጫ:- ቤተ ክርስቲያናችን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባለው አምልኮ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅና በመታዘዝ፣ ወንጌልን በትጋት በማሰራጨትና ማኅበረሰቡን በፍቅር በማገልገል እግዚአብሔርን እንድታከብር እንፈልጋለን::</td></tr>
<tr><td>ንዑስ ራእይ:- አማኞች ሁሉ ለማኅበረሰቡ በትጋት ይመሰክራሉ፣ ወንጌሉን በዓለም ውስጥ ለማሰራጨት ገንዘብ ይሰጣሉ::</td><td>ንዑስ ራእይ:- አማኞች ሁሉ በእውነትና በመንፈስ ያመልካሉ::</td><td>ንዑስ ራእይ:- አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ ይታዘዛሉ::</td></tr>
<tr><th>ውስን ግቦች</th><th>ውስን ግቦች</th><th>ውስን ግቦች</th></tr>
<tr><td>1. ጳጉሜ ውስጥ አማኞች ሁሉ ስለ ወንጌሉ ምንነት የሚያሳውቅ ሥልጠና ይሰጣቸዋል::<br>2. በመስከረም 30 አማኞች ሁሉ እምነታቸውን የተለያዩ ሃይማኖቶችን ለሚከተሉ ሰዎች ጋር በተሳበለ መንፈስ እንዴት ማካፈል እንዳለባቸው ያውቃሉ::<br>3. በጥቅምት 15 በምስክርነት ቡድኖች ይከፋፈላሉ::<br>4. በጥቅምት 30 ምስክርነት የሚሰጡባቸውን ቀናት ይወስናሉ::<br>5. በሕዳር 30 ሁሉም አማኞች ወንጌላውያንን ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለመላክ የሚያስችል ገንዘብ ይሰጣሉ::<br>6. በመስከረም 2001 ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚላኩ ወንጌላውያን ይሠለጥናሉ::</td><td>1.<br>2.<br>3.<br>4.</td><td>1.<br>2.<br>3.<br>4</td></tr>
</table>



የመጀመሪያው ሠንጠረዥ መሪው ትልቁን የቤተ ክርስቲያን ራእይ በንዑሳን ራእዮች እንዲከፋፍል ያስችለዋል:: ራእዩን እውን ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ትልቁን ራእይ በብዙ ንዑሳን ራእዮች መከፋፈል አለብህ:: ይህ ማለት የመጀመሪያውን ሠንጠረዥ በማስፋት ሁለት ወይም ሦስት ገጾች ማድረግ አለብህ ማለት ሊሆን ይችላል:: ይህ ሠንጠረዥ መሪው ዋናውንና ንዑስ ራእዮችን በመመልከት የንዑሳን ራእዮቹ ድምር ዋናውን ራእይ እንደሚፈጽም እንዲገነዘብ ያስችለዋል:: እያንዳንዱን ንዑስ ራእይ ለመፈጸም የሚያስችሉትንም ውስን ግቦች ይዘረዝራል:: ለእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ የተለያዩ ውስን ግቦችን በመዘርዘር ንዑሳን ራእዮቹ ሚዛናዊ እንዲሆኑ ያደርጋል::

በሠንጠረዡ የመጀመሪያ ረድፍ ላይ፣ ለቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም መጀመር ለምትፈልገው አገልግሎት ዐቢይ የራእይ መግለጫ ትጽፋለህ:: በሁለተኛው ረድፍ፣ ለእያንዳንዳቸው ዐበይት ክፍሎች የንዑስ ራእይ መግለጫ ትዘረዝራለህ:: በሦስተኛው ረድፍ፣ የአገልግሎቱን ንዑስ ራእዮች ለመፈጸም ይጠቅሙኛል የምትላቸውን ውስን ግቦች ትዘረዝራለህ::

ሠንጠረዥ 2:- በሠንጠረዥ 1 ውስጥ የገለጽከውን ንዑስ ራእይ፣ ውስን ግቦች፣ ዝርዝር ተግባራት፣ የጊዜ ሰሌዳ፣ ኃላፊነት የተሰጠው ሰውና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝር:-

ሁለተኛው ሠንጠረዥ የመጀመሪያውን ሠንጠረዥ ያስፋፋዋል:: እያንዳንዱ ንዑስ ራእይ የራሱ ሠንጠረዥ ያስፈልገዋል::

***የንዑስ ራእይ መግለጫ፡-*** *አማኞች ሁሉ ለማኅበረሰባቸው በትጋት ይመሰክራሉ፣ ወንጌሉን በዓለም ውስጥ ለማለራጨት ገንዘብ ይለግሉ።*

| ውስን ግቦች | ዝርዝር ተግባራት | የጊዜ ሰሌዳ | ኃላፊነት የተሰጠው ሰው | የሚያስ ፈልጉ ነገሮች |
|---|---|---|---|---|
| **1ኛ ግብ፡-** ጳጉሜ ውስጥ አማኞች ሁሉ ስለ ወንጌሉ ምንነት የሚያሳውቅ ሥልጠና ይሰጣቸዋል። | 1. የስብሰባ ቀናትን መወሰን | ሰኔ 15 | ሽማግሌዎች | |
| | 2. ተናጋሪዎችን መምረጥ እና መጋበዝ | ሰኔ 30 | ሰብሳቢው | ትራንስ ፖርትና ስጦታ=200 ብር |
| | 3. የምግብ ኮሚቴ መምረጥ | ሐምሌ 1 | ሰብሳቢው | |
| | 4. የሥልጠና መጻሕፍት መግዛት | ሐምሌ 15 | ሀብታሙ | 200 ብር |
| | 5. ለምግብ የሚያስፈልጉትን ነገሮች መግዛት | ሐምሌ 20 | ዘሪሁን | 200 ብር |
| **2ኛ ግብ፡-** በመስከረም 30 አማኞች ሁሉ እምነታቸውን የተለያዩ ሃይማኖቶችን ለሚከተሉ ሰዎች ጋር በተ ላበሰ መንፈስ እንዴት ማካፈል እንዳለባቸው | 1. | | | |
| | 2. | | | |
| | 3. | | | |
| | 4. | | | |
| | 5. | | | |
| **3ኛ ግብ፡-** | 1. | | | |
| | 2. | | | |
| | 3. | | | |
| | 4. | | | |
| **4ኛ ግብ፡-** | 1. | | | |
| | 2. | | | |
| | 3. | | | |
| | 4. | | | |



ሀ. በመጀመሪያው ዓምድ፣ በመጀመሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ የዘረዘርካቸውን ውስን ግቦች በሙሉ ጻፍ። ለምሳሌ፣ ከላይ እንደተመለከተው አምስቱን የወንጌል ስርጭት ግቦች ልትጽፍ ትችላለህ።

ለ. በሁለተኛው ዓምድ፣ ውስን ግቦቹን ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር ተግባራት ጻፍ።

ሐ. በሦስተኛው ዓምድ፣ ተግባሩ የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ጻፍ። (ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ ተመልከት።) እነዚህን ዝርዝር ተ ግባራትና የሚከናወኑባቸውን ቀናት መጻፍ ሰብሳቢው መቼ ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያውቅና ምእመናን እምነታቸውን የሚያካፍሉበትን ዘዴ የሚማሩበት ሂደት በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ይረዳዋል።

መ. በአራተኛው ዓምድ፣ የተጠቀሰውን ተግባር የመፈጸም ኃላፊነት የተሰጠውን ቡድን ወይም ግለሰብ ስም ጻፍ።

ሠ. በአምስተኛው ዓምድ ውስጥ፣ ለተጠቀሰው ተግባር የሚበቃውን ገንዘብ ተምን። አንዳንድ ጊዜ ምንም ገንዘብ ላያስፈልግ ይችላል። ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድን ተግባር ለማከናወን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ መመደብ ሊያስፈልጋት ይችላል። ሽማግሌዎች በጠቅላላው ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ለማወቅ ከፈለጉ፣ በዚህ ዓምድ ውስጥ ያሉትን የገንዘብ መጠኖች መደመር ይኖርባቸዋል።

ለሁሉም ራእዮች፣ ንዑሳን ራእዮች፣ ውስን ግቦችና ዝርዝር ተ ግባራት ይህንን አሠራር ብትከተል፣ በጣም ግልጽ የሆነ ዕቅድ ይኖርሃል። ይህ ደግሞ ለክትትልም ሆነ ወደ ራእይህ የምታደርገው ጉዞ በጥሩ ሁኔታ እየተፋጠነ መሆኑን ለመገምገም ያስችልሃል።

15ኛ ጥያቄ፡- እነዚህን ሠንጠረዦች ተመልከትና ያዘጋጀኸውን ዕቅድ ከልስ። ሀ) ሠንጠረዡ ዕቅድህን በቀላሉ እንድታዘጋጅ እንዴት እንደሚ ረዳህ ግለጽ። ለ) በዕቅድህ ውስጥ ብዙ ስፍራ ያልሰጠኸው ነገር ምንድን ነበር?

**ደረጃ ስድስት:-** የዕቅዱን አፈጻጸም ከጊዜ ወደ ጊዜ መገምገም::

ሰሎሞን ሰው እንደሚያቅድና እግዚአብሔር እንደሚፈጽም ተናግሯል:: (ምሳሌ 16:19ን አንብብ::) በሕይወት ውስጥ ከእኛ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ:: ሰዎች ለዕቅዳችን ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጡ አናውቅም:: እግዚአብሔር በተወሰነ አቅጣጫ እንዲያድጉ የሚፈልግ መሆኑን ለመረዳት ምእመናን የተወሰነ ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል:: ወይም ደግሞ እንደ ድርቅና የአዝመራ ውድመት የመሳሰሉ ነገሮች ሊከሰቱና ከዚህ ጋር ተያይዞ የገንዘብ እጥረት ሊፈጠር ይችላል:: ወይም ደግሞ ከእኛ ጋር ያገለግላል ብለን ተስፋ ያደረግነው ሰው አካባቢውን ቀይሮ ሊሄድ ይችላል:: ወይም ደግሞ ባልተጠበቀ ሁኔታ የሠለጠኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእኛ ጋር ለመሥራት ከሌላ አካባቢ በመምጣታቸው ከታቀደው በላይ ልናከናውን እንችላለን:: ልንቆጣጠራቸው የማንችላቸው ብዙ ነገሮች ስላሉ፣ ዕቅዶቻችንን በትሕትና ማውጣት አለብን:: ያዕቆብ እንዳስጠነቀቀን፣ ዕቅዶቻችንን ማዘጋጀት ያለብን «እግዚአብሔር ቢፈቅድ» በሚል አስተሳሰብ ነው (ያዕ. 4:15)::

ሁኔታዎችን መቆጣጠር ስለማንችል፣ እግዚአብሔር ምን እያደረገ እንደ ሆነና ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ ለመረዳት በየጊዜው ዕቅዶቻችንን መገምገም ይኖርብናል:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከጠበቅነው ፈጥኖ ይነሣና ለአንድ ዓመት ያቀድነው ነገር በጥቂት ወራት ውስጥ ይፈጸማል:: እኛ የዕቅዶቻችን ባሪያዎች አይደለንም:: ይልቁንም፣ ዕቅዶቻችን በዕድገት እንድንቀጥል ሊመሩን ይገባል:: ዕቅዶችን በምናዘጋጅበት ጊዜ፣ ለመፈጸም የምንፈልገው ራእይ እምብዛም እንደማይለወጥ ማወቅ አለብን:: ከራእዮች በላይ የሚለወጡት ውስን ግቦች ናቸው:: ይህም የሚሆነው ሥራውን በምንጀምርበት ጊዜ የረሳናቸውን ነገሮች ስለምናይ ወይም አስፈላጊዎች ናቸው ብለን ያሰብናቸው ነገሮች ስለሚለወጡና አስፈላጊነታቸው ስለሚቀንስ ነው:: ለዚህ ነው ከራእያችን በላይ ያቀድናቸው ውስን ግቦች የሚለወጡት:: ውስን ግቦችን ለመፈጸም የምናደርጋቸውን ነገሮች ስለምናስተካክል፣ ዝርዝር ተግባራት ብዙ ጊዜ ይለወጣሉ:: በተደጋጋሚ ግምገማ ማካሄዱ ዕቅዳችንን በተሻለ ሁኔታ ለመፈጸም ውስን ግቦቻችንን እና ዝርዝር ተግባሮቻችንን እንድንለውጥ ይረዳናል::



1. አንድ መሪ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ሦስት ዓይነት ግምገማዎች አሉ::

ሀ. ዕቅዱ እያደገ ሲሄድ የሚካሄድ <u>ቀጣይነት ያለው ግምገማ</u>:: ምንም እንኳን መሪው ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ሥራዎችን ለሌሎች በውክልና ቢሰጥም፣ ሥራው በጥራት እየተካሄደ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት:: ይህንንም የሚያደርገው ከዕቅዱ አንጻር የተከናወነውን ሥራ ቀጣይነት ባለው መልኩ በመገምገም ነው:: መሪው ከፊቱ ባለው ዕቅድ በመታገዝ፣ ነገሮች እንዴት ወደ ፊት እየተጓዙ እንደ ሆነ ለመመልከት የራእዩን ግቦችና ተግባራት በማጤን ክትትል ማድረግ አለበት:: ዕቅዱ ተግባራዊ እየሆነ አለመሄዱ ከተረጋገጠ፣ ሽማግሌዎችና በሥራው ላይ የተሳተፉት ሰዎች ችግሩ ምን እንደ ሆነ መመርመር ይኖርባቸዋል:: ይህ ውስን ግቦች ተግባራዊ እንዲሆኑና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ራእይ እንድታድግ ያስችላታል::

ለ. <u>ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደረግ ግምገማ</u>:: ይህ መሪዎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተከናወኑትን ተግባራት በጥንቃቄ የሚገመግሙበት ነው:: ይህ ግምገማ የሚካሄደው በየዓመቱ፣ በየሁለት ዓመቱ ወይም መሪዎች በወሰኑት በየትኛውም የጊዜ ገደብ ሊሆን ይችላል:: በአጠቃላይ ግን፣ እንገልግሎቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ አጭር ከሆነ፣ ተደጋጋሚ ግምገማ ያስፈልገዋል:: በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ኮንፍረንስ የሚደረግ ከሆነ፣ ኮንፍረንሱ ሊጀመር አንድ ወር ሲቀረው መሪዎች ዕቅዱ እንዴት እየሄደ እንዳለ መገምገም ይኖርባቸዋል:: ከዚያም አንድ ሳምንት ሲቀረው ተጨማሪ ግምገማ ሊደረግና ነገሮች ሁሉ በሚገባ መጠናቀቃቸው ሊታወቅ ይገባል:: ነገር ግን ራእዩ የረዥም ጊዜ ከሆነ፣ ምናልባትም በዓመት አንድ ጊዜ ግምገማ ማካሄዱ ቤተ ክርስቲያኒቱ እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ ወደ መፈጸሙ

አቅጣጫ በምን ዓይነት ሁኔታ እየተጓዘች እንዳለ ለመከለስ ያስችላል:: ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚካሄድ ግምገማ ዓላማ ምን ዓይነት ዕድገት እየታየ እንዳለና በዕቅዱ ውስጥ ምን ዓይነት ለውጥ መደረግ እንዳለበት መረዳት ነው:: ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚካሄድ ግምገማ ሁለት አቅጣጫዎችን ይመለከታል:-

1) ምን ዓይነት ነገሮች እንደ ተካሄዱና እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም በታቀደው መሠረት እየተንቀሳቀስን መሆናችንን ለመመልከት ያለፈውን ሂደት ይገመግማል:: ቤተ ክርስቲያን ያደገችው በምን በምን አቅጣጫዎች ነው? ዕቅዶቹ ስኬታማ ያልሆኑት የቱ ጋ ነው? አንዳንድ ተግባራት እንደ ጠበቅናቸው ያልተከናወኑት ለምንድን ነው? በዚህ ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ የተንቀሳቀሰበት አካባቢ የትኛው ነበር? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራችን ዕቅዳችንን ተግባራዊ ማድረግ ሳይሆን፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመንቀሳቀስ እርሱ የሚፈልገውን ማድረግ ነው:: ብዙውን ጊዜ እርሱ የሚፈልገው ምን እንደ ሆነ ቀድሞውኑ ማወቅ ሊያስቸግር ይችላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያለፈውን ሁኔታ መለስ ብለው በመመልከት፣ «ካለፈው የምንማረውና ወደፊት እንዲፈጸም ለምንፈልገው ተግባር ትምህርት ሊሰጠን የሚችል ምንድን ነው?» ብለው ይጠይቃሉ::

2) ወደፊት በመመልከት ዕቅዱን እንደገና ያስተካክለዋል:: የግምገማ ዋና ዓላማ ስለ ተበላሸው ነገር አንዱ ሌላውን የሚወቅስበትን አጋጣሚ መፍጠር አይደለም:: ይልቁንም፣ ከተገኘው ውጤት ትምህርት ማግኘትና ዕቅዳችንን የእግዚአብሔር መንፈስ ባሳየን መንገድ ማስተካከል ነው:: እርሱ በቤተ ክርስቲያናችን እና በሕይወታችን መሥራት ይፈልጋል::

ሐ. በዕቅዱ ፍጻሜ ላይ የሚደረግ ግምገማ:: ምንም እንኳን ምን ጊዜም የማይጠናቀቁ አንዳንድ የረዥም ጊዜ ዕቅዶች ቢኖሩም (ለምሳሌ፣ ክርስቶስን በመምሰል ማደግ)፣ ተሠርተው የሚያልቁ ብዙ ዕቅዶችም አሉ:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መገንባት፣ አዲስ ቤተ ክርስቲያን መትከል፣ ኮንፍረንስ ማዘጋጀት፣ ለምእመናን ስለ ወንጌል ስርጭት የሥልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ወዘተ. . .



በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚጠናቀቁ ተግባራት ናቸው:: እንድ የአጭር ጊዜ ራእይ በሚጠናቀቅበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክንውኑን መገምገም አለባቸው:: አሁንም፣ የዚህ ግምገማ ዓላማ በጥሩ ሁኔታ ስላልተከናወኑት ተግባራት ሰዎችን መውቀስ ሳይሆን፣ በሚቀጥለው ጊዜ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መሥራት እንደሚቻል ካለፈው ተሞክሮ መማር ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ «በዕቅዳችን ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተከናወነው ምንድን ነው? በጥሩ ሁኔታ ያልተከናወነውስ? ለምን? በሚቀጥለው ጊዜ የተሻለ ተግባር ለማከናወን ምን ልናደርግ እንችላለን?» የሚሉትን ጥያቄዎች አንሥተው መወያየት አለባቸው:: በተጨማሪም፣ ይህ የተለያዩ ሰዎች እንዴት የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንደ ተወጡ ለመመልከት የሚችሉበት ጥሩ አጋጣሚ ነው:: እነዚህ ሰዎች ያሳዩአቸው ችሎታዎችና መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን ምንድን ናቸው? እነዚህን ችሎታዎችና ስጦታዎች እንዴት ማሳደግ ይቻላል? ያ ግለሰብ በሚቀጥለው ጊዜ ተጨማሪ ኃላፊነት ሊሰጠው ይገባል? ሰዎች ተግባራቸውን በሚገባ ካልተወጡ፣ ይህ የሆነው ለምንድን ነው? ይህ የሆነው ውክልናው ጥሩ ስላልነበረ ነው ወይስ ግለሰቦቹ ተነሣሽነት ስላነሳቸው? እነዚህ ሰዎች በሙሉ ኃይላቸውና ልባቸው እግዚአብሔርን ማገልገል ይችሉ ዘንድ መሪዎች እንዴት ሊረዷቸው ይችላሉ?

ግምገማ ካላካሄድን፣ ለውድቀት የዳረጉንን ነገሮች ደግመን እንደምንፈጽም መዘንጋት የለብንም:: መውደቅ ክፋት የለውም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ከውድቀታችን በመማር ወደ ፊት በእስተዋይነት እንድናድግ ይፈልጋል:: የተከሰተውን ነገር መገምገም ስሕተቶቻችንን እንዳንደግምና በእስተዋይነት እንድናድግ ይረዳናል:: ማንም ሰው ውጤታማ የማይሆኑትን ነገሮች ሊሞክር ይችላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንድን ነገር ለመሞከር ከፈሩ፣ በእምነት ሊመላለሱ ወይም እግዚአብሔር እንድናደርግ ይፈልጋል ብለው የሚያምኑትን ነገር ሊያደርጉ አይችሉም:: የምናውቀውን ብቻ ስንሠራ ብንኖር፣ ልናድግ አንችልም:: መጀመሪያ ስንሞክር ያልተሳካልንን ነገር ማድረጋችን ሞኝ አያስብለንም:: ነገር ግን መጀመሪያ ያልተሳካልንን ነገር ለሁለተኛ ጊዜ ከደገምን፣ ሞኞች

ነን። አንድ ነገር ለምን ውጤታማ ሳይሆን እንደ ቀረ ካልገመገምን፣ በቀጣዩም ጊዜ ያንኑ ስሕተት በመፈጸም ከውጤታማነት ልንርቅ እንችላለን።

2. አገልግሎቶችን የምንገመግመበት ሦስት ዐበይት ምክንያቶች አሉ። <u>በመጀመሪያ</u>፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም የምንጥርበትን መንገድ ለማሻሻል እንፈልጋለን። <u>ሁለተኛ፣</u> በቀጣዩ ጊዜ እንዴት ነገሮችን በተሻለ መንገድ እንደምናከናውን ለመማር እንፈልጋለን። ሁልጊዜም መሻሻል የሚቻልባቸው መንገዶች አሉ። ይህም መሻሻል ሊመጣ የሚችለው ከግምገማ ነው። ሦ<u>ስተኛ</u>፣ ስጦታቸው ምን እንደ ሆነ፣ ለእግዚአብሔር የተሻለ አገልግሎት ይሰጡ ዘንድ እንዴት ልንረዳቸው እንደምንችልና ተጨማሪ ኀላፊነት ልንሰጣቸው እንችል እንደ ሆነ ለማየት ሰዎችን እንገመግማለን። እግዚእብሔር የሰዎችን የኀላፊነት ደረጃ የሚጨምረው ሁልጊዜም በትናንሽ ነገሮች በመፈተን ነው። ተጨማሪ ኀላፊነቶችን የምንሰጣቸው ታማኞችና ችሎታ ያላቸው መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነው። ሰዎች በሥራቸው ታማኝነታቸውን ማረጋገጣቸውንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጨማሪ ኀላፊነት ልንሰጣቸው አንችል እንደ ሆነ የምናውቀው ግምገማ በማካሄድ ነው።

(ማስታወሻ፡- «ውክልና» የሚለው ቃል በሁለት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል። <u>የመጀመሪያው</u>፣ አንድ ሰው *በማይኖርበት ጊዜ* ለሌላ ሰው ኀላፊነቱን በመስጠት የተወሰነ ሥራ እንዲያከናውን የሚያደርግበትን ሁኔታ ያሳያል። ሊቀ መንበሩ ወደ ሌላ ቦታ ቢሄድ ም/ሊቀ መንበሩ ቦታውን ተክቶ እንዲሠራ ይወክለዋል። በአካባቢው ካለ ግን ሊቀ መንበሩ ሥራውን ያከናውናል። <u>ሁለተኛ</u>፣ አንድ ሰው እዚያው *እያለ* ከኀላፊነቱ ቀንሶ ለሌላ ሰው በመስጠት በእርሱ ክትትል ሥር ሆኖ እንዲሠራ ሊያደርግ ይችላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንጠቀምበት ይህንኑ የውክልና ዘዴ ነው። በቀጣዩ ሳምንት ስለ ውክልና በደንብ እንማራለን።)



የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምእመናንን መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚያውቁትና ወደ ፊት በምን ዓይነት አገልግሎቶች ላይ ሊያሰማሯቸው እንደሚገባ የሚገነዘቡት ኀላፊነቶችን በውክልና ከሰጧቸው በኋላ አፈጻጸማቸውን በቅርበት በመከታተል ነው። ይህ ሰዎች ለእግዚአብሔር በሚሰጡት አገልግሎት እንዲያድጉ የምንረዳበትን መንገድ ያሳየናል። በመሆኑም፣ ግምገማ ለእግዚአብሔር በምንሰጠው አገልግሎት አንድናድግ ከፍተኛ እሴተ ዋጽኦ ያደርግልናል። ዳዊት እንደ ገለጸው፣ «ጻድቅ ሰው ይቅጣኝ፣ ይገሥጸኝም፤ ይህ በጎነት ነው፤ በራሴ ላይ እንደሚፈስ ዘይት ነው፤ ራሴም ይህን አንቢ አይልም። ጸሎቴ ግን በክፉዎች ተግባር ላይ ነው» (መዝ. 141:5)። ዳዊት ለማለት የፈለገው ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በውጤታማነታቸው ሊያድጉ የሚችሉት የሚያርማቸውና የሚመክራቸው መንፈሳዊ ሰው ሲኖር መሆኑን ነው። እርማት የፍቅር ምልክት እንጂ፣ ቸል ሊባል የሚገባው ነገር አይደለም። የግምገማ ግቡም ይኸው ነው። ነገር ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን እና እንደ ግለሰቦች እንዲህ ዓይነቱን ግምገማ ለመቀበል ትሕትናንና የማደግ ፍላጎትን ይጠይቃል።

16ኛ ጥያቄ፡- በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የምታከናውነውን አንድ ሥራ ጥቀስ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ይህንኑ ሥራ ገምግም። ሀ) በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑ ያሉት ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ለ) በጥሩ ሁኔታ የማይከናወኑ ወይም ውጤታማ ያልሆኑ ነገሮችስ የትኞቹ ናቸው? ሐ) የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማሻሻል የምትችልባቸው መንገዶች ምን ምንድን ናቸው?

17ኛ ጥያቄ፡- ቀደም ሲል የተሳተፍክበትንና አሁን ግን የተጠናቀቀን አንድ ሥራ ጥቀስ። ሀ) በዚያ ሥራ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተከናወነው ምን ነበር? ለ) እንደገና ያንን ሥራ ብታከናውን፣ የተሻለ ውጤት ለማግኘት አሁን እንዴት በተለየ ሁኔታ ታከናውነው ነበር? ሐ) በሚቀጥለው ጊዜ ያ አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ውጤታማ እንዲሆን አንተ ወይም ሌሎች ሰዎች በምን ምን አቅጣጫዎች ማደግ ይኖርባችኋል? መ) በሚቀጥለው ዓመት በዚህ አገልግሎት በኩል የበለጠ ለማደግ ምን ልታደርግ ትችላለህ?

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለቤተ ክርስቲያን እያዘጋጀህ ያለኸውን ዕቅድ ተመልከት:: ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ቀጣይነት ያለው አገልግሎት በሚያካሂድበት ጊዜ ምን ምን ነገሮችን ማድረግ ያለበት ይመስልሃል? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ግምገማ በሚያደርጉበት ጊዜ በምን ምን ነጥቦች ላይ ማተኮር የሚገባቸው ይመስልሃል? ሐ) ከውስን ግቦች አንዱ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ግምገማ የምታደርግበት ቢሆን፣ ግምገማው በሥራው ውስጥ ለተሳተፉት ወገኖች የመማሪያ መድረክ ይሆን ዘንድ የግምገማውን ተግባር እንዴት ታከናውን ነበር?

እንደ ተመለከትነው፣ አመራር «ክህሎትን» ያካትታል:: በልምምድ እንደምናገኛቸው ማናቸውም ነገሮች፣ እንዲህ ዓይነቱን ዕቅድ ማዘጋጀት መጀመሪያ ሲታይ ከባድ ይመስላል:: ይህ ጊዜን፣ ማሰላሰልንና ብዙ ጸሎትን የሚጠይቅ ሥራ ነው:: ነገር ግን በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተዘጋጀ ዕቅድ እግዚአብሔር ወደ ሰጠን ራእይ በፍጥነት ያደርሰናል:: እነዚህን ደረጃዎች ተከትለን በምንሠራበት ጊዜ፣ ወይም ደረጃዎቹን በክትትል መልክ በምንመለከትበት ጊዜ፣ ከባድ ሥራ እንደሚጠብቀን ግልጽ ነው:: እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ እንደ ድሮዬ በሠራሁት ልንል እንችላለን:: ይሁንና፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ክህሎቱን እየተካንን ስንመጣ፣ ሂደቱ ቀላል ይሆናል:: በመጨረሻም፣ በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀ ዕቅድ የኋላ ኋላ ጊዜ የሚቆጥብልን መሆኑን እንረዳለን::

ከአንድ ወይም ሁለት ወራት ቀደም ብሎ እነዚህ የዘረዘርናቸው ደረጃዎች ተከናውነው ቢሆን ኖሮ፣ በአንደኛው ቀን የተገለጸውን ኮንፍረንስ ያዘጋጁት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደስ በተሰኙ ነበር:: ስለዚህ፣ ይህንን የጥሩ ዕቅድ ክህሎት ልንማር ይገባል:: ይህ ሽማግሌዎች ለእግዚአብሔር ክብር በውጤታማነት የሚሠሩ እውነተኛ «መሪዎች» እንዲሆኑ ያግዛቸዋል:: ቤተ ክርስቲያናቸው እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ስፍራ እንድትደርስ የሚያግዝ እርምጃ እየወሰዱ መሆናቸውን በሚመለከቱበት ጊዜ ይበረታታሉ::

## **ሦስተኛ ቀን**

አንዳንድ ሰዎችና አብያተ ክርስቲያናትን ከሌሎች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? በቀዳሚነት መንፈስ



ቅዱስ ለመሥራት መምረጡ ነው:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ሰዎችን ከሌሎች የበለጠ የሚጠቀም የሚመስለው ለምንድን ነው? በመጀመሪያ፣ እነዚህ ሰዎች፣ እንደ ዳዊት፣ እግዚአብሔርን የሚወዱና እርሱን ለማገልገልና ለማክበር የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው:: እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋፋት የሚጠቀምበት ባሕርይ እንዲኖረን ከተፈለገ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው ሆኖ መገኘት ወሳኝ ነው:: እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር የአመራር ክህሎት ያላቸውን ሰዎች በሚገባ ይጠቀማል:: አንድ ሰው፣ እንደ ነህምያ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል በመፈለግ ጥሩ ዕቅዶችን በሚያወጣበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለክብሩ ታላላቅ ነገሮችን ሊያከናውኑ ይችላሉ::

መንፈስ ቅዱስ ታላቅ ተግባር ለማከናወን የሚጠቀምበትን ዕቅድ ማውጣት ሁለት ዐበይት ነገሮችን እንደሚያካትት ተመልክተናል:: የመጀመሪያው፣ ራእይ ወይም ምእመናንን የምንመራበት ዐቢይ ግብ ወይም ዓላማ ማግኘት ነው:: ሁላችንም እግዚአብሔር ለምን እንደ ፈጠረንና ለክብሩ ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ማወቅ አለብን:: እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ልዩ ራእይ ለእርሷ እንደ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደ ሆነ ማወቅ አለባት:: ይህ ሥራችን በሚጠናቀቅበት ጊዜ ምን እንደሚመስል ተረድቶ የመጀመሩ እውነታ በዕቅዶቻችን ውስጥ ወሳኝ ነው:: ጥሩ ዕቅድ መውጣት የሚጀምረው የመጨረሻ ግቡ ምን እንደ ሆነ ከመወሰን ነው:: ስለሆነም፣ አንድ **መሪ ሊያሳድገው የሚገባው የመጀመሪያው ክህሎት ሕዝቡን ወዴት እንደሚመራ** ማወቅ ነው:: ይህ ራእይ ያለው መሪ የመሆን ክህሎት ነው::

የትኛውም ራእይ በራሱ ሰውጥ ሊያመጣ አይችልም:: ራእዩ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወይም ግለሰቡን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራእይ ወደ መፈጸሙ ወደሚመራ ዕቅድ መቀየር አለበት:: **ሁለተኛው የአመራር ክህሎት እግዚአብሔር ለመሪውና ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ እውን የሚያደርግ ጥሩ ዕቅድ ማውጣት ነው::** ቀደም ሲል ራእዩን ለመፈጸም መከናወን ያለባቸውን የተለያዩ

ውስን ግቦች በመዘርዘር ዕቅድ አውጥተናል። ከዚያም እያንዳንዱን ውስን ግብ በተለያዩ ተግባራት እንከፋፍላለን። እነዚህ ተግባራት ግቦቹን እውን የሚያደርጉ ናቸው። እነዚህ የተግባር ደረጃዎች ማን የትኛው ተግባር ላይ እንደሚሰማራና ተግባሩ ከፍጻሜ ይደርስ ዘንድ የትኞቹ ቁሳቁሶች ወይም ገንዘብ መሟላት እንዳለበት የሚያሳዩ ናቸው። ራእዩ ትንሽም ይሁን ትልቅ፣ እግዚአብሔር ለግለሰብም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ለመፈጸም እነዚህ ደረጃዎች መሟላት አለባቸው። ይህ ዕቅድ የማውጣቱ ሂደት በአጠቃላይ መልኩ በአስተዳደር ሥር የሚውል ነው። ይህ መሪው ወደሚፈልገው አቅጣጫ ለመምራት መሻት ነውና።

ጥሩ ዕቅዶችን ማውጣት ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትም ሆነ ማንኛውንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ለማከናወን በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣ ዛሬ እንዴት ጥሩ ዕቅድ ማውጣት እንደሚቻል እናጠናለን። በዚህ ትምህርት ውስጥ ሁለት ዕቅዶችን ታዘጋጃላችሁ። አንዱ የግል፣ ሁለተኛው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል። ለቤተ ክርስቲያን ዕቅድ በምታወጡበት ጊዜ ልታስታውሷቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፦

## ጥሩ ዕቅድ እንዲኖረን ከተፈለገ፣ ዕቅድ የሚያወጡትን ሰዎች በጥንቃቄ መምረጥ አለብን

ወደ ገበያ ሄደን በሬ ስንገዛ፣ ወይም ሱቅ ሄደን ቴፕ ወይም የሲዲ ማጫወቻ ስንገዛ፣ የምንገዛውን ነገር ጥራት በሚገባ እንፈትሻለን። ባለን ገንዘብ ምርጥ በሬ፣ ወይም ቴፕ ወይም የሲዲ ማጫወቻ ለመግዛት እንፈልጋለን። እንዲሁም ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ በምንሠራበት ጊዜ፣ ሥራውን ለማከናወን የሚችሉ ምርጥ ሰዎች ያስፈልጉናል። የወንጌላዊነት ስጦታ ወይም ሥልጠና የሌለውን ሰው ለወንጌላዊነት መምረጥ፣ ወይም ፈቃደኛ ስለሆነ ብቻ ማንኛውንም ሰው ለመጋቢነት አገልግሎት መቀበል፣ ከእግዚአብሔር ሥራ ይልቅ ለራሳችን ሥራ እንደምንጨነቅ ያሳያል። በምድር ላይ ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም ብቃት ያላቸው ሰዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ ማድ



ረጉ እጅግ ወሳኝ ነው። ዕቅዱን ከፍጻሜ ለማድረስ ያሉንን ምርጥ ሰዎች መጠቀም አለብን።

ጥራት ያላቸውን ዕቅዶች ለማውጣትና እነዚህን ዕቅዶች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ከፈለግን፣ በመምራትና ውክልና በመስጠት መካከል ያለውን ግንኙነት ማወቅ አለብን። ዕቅዶችን በሚያወጡበት ጊዜ፣ መሪዎች ሁለት ዐበይት ኃላፊነቶችን ይወጣሉ። በመጀመሪያ፣ ዕቅዶችን የሚያዘጋጁት በጥበብ ዕቅዶችን የሚያወጡና ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች በመምረጥ ነው። ሁለተኛ፣ መሪዎች የዕቅዶቹን ዝግጅትና ክንውን ይከታተላሉ። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራ ስለሚበዛባቸው ጥሩ ዕቅድ የማውጣቱን ረዥምና እድካሚ ሂደት ለማከናወን ይቸገራሉ። የግል ሥራቸውን በማከናወንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱትን ከባባድ ችግሮች ለመፍታት ወዲያና ወዲህ ስለሚሯሯጡ የጊዜ እጥረት ይገጥማቸዋል። ስለዚህ ሥራውን በሰዎች በኩል ማከናወንን መማር አለባቸው። (ማስታወሻ፦ ወደ በኋላ ስለ ውክልና ክህሎት እንማራለን።)

> 19ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት የሚቸገሩት ለምን ይመስልሃል? ለ) ቁልፍ መሪዎች ያልሆኑ አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያህል ሥራ ስሱ-ማይበዛባቸው ዕቅዶችን ጥሩ አድርገው ሲያዘጋጁ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ።

ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ራእይ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ራእዩ እውን እንዲሆን ከተፈለገ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዕቅድ ዝግጅቱን ሂደት በሚገባ መከታተል አለባቸው። ከዚህ በታች ሽማግሌዎች የዕቅድ ዝግጅት ሂደት በሚከታተሉበት ጊዜ ሊያከናውኗቸው የሚገባቸው አንዳንድ ነጥቦች ተዘርዝረዋል።

1. ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ እውን ለማድረግ ጥራት ያለው ዕቅድ የማዘጋጀቱን ሂደት የመጀመር ኃላፊነት አለባቸው።

ሀ. ሽማግሌዎች መጀመሪያ ራእዩን ግልጽ በማድረጉ ላይ ማተኮር አለባቸው። ሁሉም መሪዎች እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ ከተገነዘቡ በኋላ፣ ራእዩ ወደ ምእመናን መተላለፍ አለበት። ምክንያቱም እነርሱም ራእዩ ከእግዚአብሔር የመጣና የእነርሱም ራእይ መሆኑን ማመን አለባቸው። ራእዩ መሪዎች ምእመናን እንዲቀበሉ የሚያዝዙት ሊሆን አይገባም። ይልቁንም፣ ምእመናን ይህ ለእግዚአብሔር ክብር ሊያከናውኑት የሚገባ የራሳቸው ራእይ እንደ ሆነ ይገነዘባሉ።

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቂ ጊዜና ችሎታ ያላቸው ሰዎች ራእዩ ተግባራዊ እንዲሆን የሚያግዝ ዕቅድ እንዲያወጡ ሊወከሏቸው ይገባል። ብዙውን ጊዜ መሪዎች እንደ ቡድን እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም የሚያስችሉ ራእዮችን ሊያዘጋጁ አይችሉም። መሪዎች ሥራ ስለሚበዛባቸው፣ ለተወሰኑ አገልግሎቶች ዝርዝር ዕቅዶችን ወይም ዐበይት ግቦችን ሊያዘጋጁ አይችሉም። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕቅድ የሚያወጡ ሰዎችን መምረጥ አለባቸው። እያሌ ዐበይት ንዑሳን ራእዮች ካሉ፣ የተለያዩ ሰዎች ለእያንዳንዱ ንዑስ ራእይ ዕቅዶችን ማዘጋጀት አለባቸው።

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትክክለኛ ሰዎች ተመርጠው ዕቅዶችን በሚያዘጋጁ ኮሚቴዎች ውስጥ እንዲመደቡ ማድረግ አለባቸው።

ጥሩ ዕቅድ ሊዘጋጅ የሚችለው ትክክለኛ ሰዎች ሊሳተፉበት ብቻ ነው። ዕቅዱን የሚያወጣው ኮሚቴ ብቃት በሌላቸው ሰዎች የተሞላ ከሆነ፣ ዕቅዱ ደካማ ይሆናል። ነገር ግን ኮሚቴው ውስጥ ያሉት ሰዎች ምርጥ ከሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ከፍ ያለ ክብር የሚያመጣ ዕቅድ እንዲያወጡ ይጠቀምባቸዋል። ፍላጎት ወይም በቂ ጊዜ የሌላቸው ሰዎች ከተመረጡ፣ ጥሩ ዕቅድ ሊዘጋጅ አይችልም። ግልጽ ዕቅድ ካልተዘጋጀ ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ ተግባራዊ ልታደርግ አትችልም። ስለሆነም፣ በኮሚቴው ውስጥ ዝርዝር ዕቅዶችን ለማውጣት የሚችሉ ሰዎች መመረጣቸው አስፈላጊ ነገር ነው።



መሪዎች ራእዩን ወደ ዝርዝር ዕቅዶች የሚለውጡ ሰዎችን ለመምረጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡-

ሀ. የቡድኑ አባላት ቁጥር አነስተኛ መሆን አለበት። ቡድኑ ብዙ ሰዎች የሚገኙበት ከሆነ፣ እያንዳንዳቸው አሳባቸውን እየገለጹ ዝርዝር ዕቅዶችን ለማውጣት የሚያስፈልገውን ጊዜ ሊያባክኑ ይችላሉ። ስለዚህ፣ ግልጽ ዕቅዶች የማውጣቱ ሥራ አራት ወይም አምስት ሰዎች ለሚገኙበት ቡድን በውክልና መሰጠት አለበት። አንዳንድ ሰዎች የኮሚቴ አባላት ቁጥር ጎደሎ መሆን አለበት ይላሉ። ይህም የአሳብ ልዩነት ከተፈጠረ በድምጽ ብልጫ ለመወሰን ያስችላል። ነገር ግን፣ የኮሚቴው አባላት በሙሉ በሳል አማኞች ከሆኑ፣ ይህ አስፈላጊ አይሆንም። አንዳንድ ሰዎች የቡድኑ አባላት በሙሉ ካልተስማሙ፣ ሥራውን አላከናውንም የሚል መርሕ ይከተላሉ። የሁሉም ሰው ስምምነት የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ምልክት ነው ብለው ያምናሉ።

ለ. ኮሚቴው ትክክለኛ ሰዎች የሚገኙበት እንዲሆን በጥንቃቄ መመረጥ አለበት፡-

1) የኮሚቴው አባላት በመንፈሳዊነታቸው የታወቁ መሆን አለባቸው። ምንም ዓይነት ዕቅድ ቢዘጋጅ፣ የቡድኑ አባላት እግዚአብሔር እንዲመራቸው በጸሎት የጠየቁት መሆኑን መሪዎቹ ማመን አለባቸው። የምንፈልገው በእግዚአብሔር ጥበብ እንጂ በሰዎች ጥበብ የተዘጋጀ ዕቅድ አይደለም። ይህ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸውና ቃሉን የሚያውቁ መንፈሳዊ ሰዎች ሥራውን ማከናወን አለባቸው ማለት ነው (የሐዋ. 6፡1-6)።

2) ኮሚቴው ውስጥ የሚገኙ ሰዎች አገልግሎቱን ተግባራዊ በማድረጉም በኩል የሚሳተፉ መሆን አለባቸው። ብዙውን ጊዜ በአገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ልምድ ስላላቸው፣ አገልግሎቱ ስኬታማ እንዲሆን መደረግ ያለበትን ነገር ያውቃሉ። ዕቅዱን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች የውይይቶቹ አካል ካልሆኑ፣ ለዕቅዱ ተግባራዊነት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሊሰጡ አይችሉም።

ይህ የእኛ ሳይሆን የሌላ ሰው ራእይ ነው የሚል አመለካከት ይኖራቸዋል።

3) ምእመናን በኮሚቴው ውስጥ እንዲሆኑ የተመረጡት ሰዎች ዕቅድ የሚያወጡባቸውን አገልግሎቶች እንደሚያውቁ መረዳት አለባቸው። አንድ ሰው ኮሚቴው ውስጥ የገባበትን ምክንያት ምእመናን ማወቅ አለባቸው። እንደዚያ ካልሆነ፣ ሕዝቡ ሽማግሌዎች ሰዎችን ኮሚቴው ውስጥ ያካተቱት በችሎታቸው ሳይሆን ስለሚወዷቸው ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ።

4) የኮሚቴው አባላት በኮሚቴው ውስጥ ለማገልገል ፍላጎት ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። ሽማግሌዎች እንዲያገለግሉ ከነገሯቸው ግን ጥራት ያለው ዕቅድ ለማዘጋጀት በትጋት ሳይሠሩ ይችላሉ። አንድ ሰው አንድ ነገር እንዲሳካ በሙሉ ልቡ የሚሠራው በፈቃደኝነት ሲስማማ ብቻ ነው።

5) የኮሚቴው አባላት የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸው መሆን አለባቸው። ሴቶችና ወንዶች፣ እንዲሁም ወጣቶችና አረጋውያን በኮሚቴው ውስጥ መታቀፍ አለባቸው። የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸው የተለያዩ ሰዎች ውሳኔዎቹን ሚዛናዊ ያደርጓቸዋል። ለምሳሌ፣ ኮሚቴው የተመደበው በቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም ዕቅድ እንዲያወጣ ከሆነ፣ በኮሚቴው ውስጥ ስለትንንሽ ልጆች፣ ስለወጣቶች፣ ስለሴቶችና ስለአዋቂዎች የሚያስቡ መሆን አለባቸው። በዚህ ዓይነት በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሊወከሉ ይችላሉ።

6) ሽማግሌዎች ሰዎችን ለኮሚቴው በሚመርጡበት ጊዜ ከአድልዎ መንጻት አለባቸው። ምእመናን ሰዎች ጓደኞቻቸውን ወይም የራሳቸውን ጎሳ አባላት እየመረጡ ነው የሚል ግምት ካላቸው፣ የተዘጋጀውን ዕቅድ ላያከብሩ ይችላሉ። ሰይጣን ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የተመረጡበትን መንገድ በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል ሊያመጣ ይችላል። ምእመናንን የሁሉንም አባላት ጥቅም ለማስከበር የሚፈልጉ ምርጥ ሰዎች በኮሚቴው ውስጥ ተካትተዋል የሚል ግምት ሊኖራቸው ይገባል።



20ኛ ጥያቄ፡- ለቤተ ክርስቲያናችሁ ጥራት ያለው የሰንበት ትምህርት ፕሮግራም የሚያዘጋጅ ኮሚቴ የማዋቀር ኃላፊነት ተሰጥቶሃል እንበል። የሰንበት ትምህርት ፕሮግራሙ በሁሉም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲሰጥ ይፈልጋል። ከላይ በተጠቀሱት ስድስት አሳቦች ላይ በመመሥረት፣ ሀ) ለኮሚቴው እነማንን ትመርጣለህ? ለ) የምትመርጣቸው ለምንድን ነው?

3. ለኮሚቴው ተጠሪ የሆነ አንድ ሽማግሌ በኃላፊነት መሰየም አለበት። ኮሚቴው ማብራሪያ፣ አስተያየት፣ ወይም ምሪት በሚፈልግበት ጊዜ ወደዚሁ ሽማግሌ በመሄድ መፍትሔ ያገኛል። ብዙውን ጊዜ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሁሉም ሽማግሌዎች ከሆነ፣ በጥሩ ሁኔታ ሥራውን ሊያካሂድ አይችልም። ምክንያቱም ኮሚቴው ማብራሪያ በሚፈልግበት ጊዜ ሁሉም ሽማግሌዎች ሳይገኙ ይችላሉ። በመሆኑም፣ ሽማግሌዎች ኮሚቴው ዕቅዶቹን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚመራው አንድ ሽማግሌ ሊመደብለት ይገባል።

ኮሚቴው ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ፣ የሚሠራው ሥራ ሽማግሌዎቹ የሚፈልጉት መሆኑን ለማረጋገጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተጠሪነት የተመደበለትን ሽማግሌ ማማከር አለበት። ለምሳሌ፣ ኮሚቴው ውስን ግቦችን ካጠናቀቀ በኋላ ሥራውን ለሽማግሌው ማሳየት አለበት። ሽማግሌው ኮሚቴው የሳተው አስፈላጊ ነገር ካለ ያስተካክላል፣ ትክክል ከሆነ ደግሞ ውሳኔውን ያጸድቃል። ከዚያም ዝርዝር ተግባራትን፣ የሚያስፈልጉትን ሰዎችና የገንዘብ መጠን ከዘረዘሩ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን መሪው ማሳየት አለባቸው። ቡድኑ ራእዩን ወደ እውነታ ለመቀየር ምን ያህል ገንዘብ እንዳለ ማወቅ አለበት። ቡድኑ ለሥራው የመረጣቸውን ሰዎች ከማነጋገሩ በፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእነዚህ ሰዎች ላይ ቅሬታ እንደሌላቸው ማጣራት አለበት።

**ዕቅድ ከሚያወጣና ተግባራዊ ከሚያደርግ ኮሚቴ ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ሽማግሌዎች የሚፈጽሟቸው ስድስት ስሕተቶች።**

ጥሩ ዕቅድ የማውጣትን ክህሎት ከመማር ሂደት አንዱ መሪዎች የሚፈጽሟቸውን ስሕተቶች በመገንዘብ እነዚህን ስሕተቶች

ላለመድገም መጠንቀቅ ነው:: ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሪዎች ከኮሚቴ ጋር በሚሠሩበት ጊዜ ከሚፈጽሟቸው ስሕተቶች የተለመዱት ናቸው:-

1. መሪው መጀመሪያው ላይ ለኮሚቴው ግልጽ መመሪያ ስለማይሰጥ ቡድኑ ሽማግሌዎቹ ምን እንደሚፈልጉ ለማወቅ ይቸገራሉ:: ሽማግሌዎቹ ግልጽ መመሪያዎችን ከሰጡ፣ ቡድኑ የቤተ ክርስቲያኒቱን ራእይ በመገንዘብ የሚጠበቅባቸውን ተግባር ይፈጽማሉ:: በመሆኑም፣ ተጠሪ የሆነው መሪ በኮሚቴው የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ በመገኘት የኮሚቴው አባላት ሁሉ ሽማግሌዎቹ ምን እንደሚፈልጉ በትክክል መረዳታቸውን ማረጋገጥ አለበት:: ይህ ተግባር መጀመሪያ በጥሩ ሁኔታ ካልተከናወነ፣ ብዙ ጊዜ ይባክናል:: ይህም የሚሆነው ኮሚቴው የሽማግሌዎቹን ፍላጎት የማያሟላ ዕቅድ ስለሚያወጡና ይህም ተቀባይነት ስለማያገኝላቸው በድጋሚ ለመሥራት ስለሚገደዱ ነው:: ቡድኑ ሽማግሌዎቹ የማይቀበሉትን ዕቅድ በማውጣት ውድ ጊዜውን ካባከነ በኋላ እርማቶች በሚደረጉበት ጊዜ በአብዛኛው የቡድኑ አባላት ስሜት ስለሚጎዳ፣ ዕቅዱን ለማስተካከልም ሆነ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ደስተኞች አይሆኑም:: በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ሽማግሌው ሊከናወን የተፈለገውን ራእይ ምንነት በሚገባ ማብራራትና ግልጽ ማድረግ አለበት:: ዕቅዱን የሚገድቡትን ማናቸውንም ቅድመ-ሁኔታዎች መግለጽ አለበት:: ለምሳሌ፣ የተወሰኑ ሰዎችን በመጠቀም ዕቅዱን ማውጣት እንደሚችሉና ተግባራዊ ሥራዎችን ለማከናወን እነማንን መጠቀም እንደሚችሉ መግለጽ አለበት:: እንዲሁም ደግሞ ዕቅዳቸውን ለመፈጸም ስንት ብር እንደ ተመደበላቸው ሊነገራቸው ይገባል::

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ መሪ አንድ ተግባር እንድትፈጽም ከጠየቀህ በኋላ በመጀመሪያ በቂ መመሪያዎችን ያልሰጠበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ይህ ምን ዓይነት ችግሮችን አስከተለ?

2. ሽማግሌው ቡድኑን ከሚገባው በላይ ይቆጣጠራል:: የተመደበው መሪ ቡድኑ ምን ማድረግ እንዳለበት ካብራራ በኋላ፣ የቡድኑ አባላት ዕቅዶቻቸውን በሚያወጡበት ጊዜ ሥራውን



ለመቆጣጠር መሞከር የለበትም:: ነገር ግን ቡድኑ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚፈልጉትን ሥራ እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ በየጊዜው ግምገማ ማድረግ አለበት:: የዕቅዱ ዝርዝር መተው ያለበት ለቡድኑ ነው:: ሽማግሌው አስተያየት መስጠት ያለበት ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እየሄዱ መሆናቸውን ወይም ሳያነሡ ያለፉት ነገር እንዳለ ከተገነዘበ ብቻ መሆን አለበት:: ሽማግሌው በቡድኑ አሠራር ደስተኛ ካልሆነ፣ አንድም በኮሚቴው ውስጥ ገብቶ በመሳተፍ ወይም ግልጽ መመሪያ በመስጠት ሊመራቸው ይገባል:: ከዚህ ውጭ የቡድኑን ሥራ መተቸቱን የሚቀጥልና በዕቅዱ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ፣ በኮሚቴው ውስጥ ያሉትን ሰዎች የፈጠራና የተሳትፎ ስሜት ሊያከስም ይችላል:: «መሪው የምንሠራውን ሁሉ ከምንም የማይቆጥር ከሆነ፣ ለምን እንደክማለን? እርሱ ሁሉንም ውሳኔ ያድርግ፤» ብለው ያስባሉ:: ሽማግሌው በዕቅዱ ዝርዝሮች ውስጥ ጣልቃ ከመግባት ይልቅ፣ ቡድኑ ከሌላ አቅጣጫ እንደገና ማሰብ እንዲችሉ የሚያደርጉትን ጥያቄዎች ቢያነሣ የተሻለ ይሆናል:: «እንዲህ ስለ ማድረግ አስባችኋል? እንዲህ ብታደርጉ፣ ያ ቡድን እንዴት ይሆናል? ለማከናወን የምትፈልጉትን ነገር ለመተግበር ከዚህ የተሻሉ መንገዶች ይኖሩ ይሆን?» የሚሉትን ዓይነት ጥያቄዎች መሪው ለቡድኑ ሊያቀርብ ይችላል::

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በኮሚቴ ወይም በቡድን ላይ ቁጥጥር ሲያበዛ ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ይህ በኮሚቴው አባላት ላይ ያስከተለው ችግር ምንድን ነበር?

ኮሚቴው ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ መሪው በሚገባ አይሳተፍም:: መሪው የቡድኑን የዕቅድ አቅጣጫ ካላወቀ፣ የተጠናቀቀውን ሥራ እንዲያጸድቁላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪዎች በሚጠይቁበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎቹም ሆኑ የኮሚቴው አባላት ለሀፍረት ይጋለጣሉ:: ሽማግሌዎቹ ዕቅዱ እነርሱ የፈለጉትን ዓላማ የማያንጸባርቅ ሆኖ ሲያገኙ ይገረማሉ:: ለምሳሌ፣ ሽማግሌዎች የፈለጉት የሰንበት ትምህርት ቤት ኮሚቴው በአነስተኛ ዋጋ ትምህርት መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ እንዲቀርጽ ይሆናል::

ቡድኑ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመጀመር የሚያስችል ዕቅድ ነድፎ ይቀርባል:: ዕቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ፣ «መሪዎች አንፈልገውም:: የወሰናችሁትን ነገር አንቀበልም» ለማለት ይቸገራሉ:: በሥራው ላይ ብዙ ጊዜ ላጠፉትና በሠሩት ሥራ ደስ ለተሰኙት የኮሚቴው አባላት እንዲህ ዓይነቱ ምላሽ ጥሩ ስሜት እንደማይፈጥር ግልጽ ነው:: የደከሙበት ሥራ ተቀባይነት ካላገኘ፣ የቡድኑ አባላት ተስፋ ስለሚቆርጡ እንደገና በዕቅዱ ላይ ለመሥራት ላይፈልጉ ይችላሉ:: የቡድኑ አመለካከት፣ «ምርጥ ሥራ ሠርተንላቸው፣ አልወደዱትም:: ሽማሌዎቹ ራሳቸው ይሥሩት» የሚል ይሆናል:: ወደ ፊት የአንድ ቡድን አካል እንዲሆኑ ከተጠየቁ፣ ከዚህ ተሞክሮአቸው የተነሣ ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ:: ዕቅዱ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደገና እንዲሠራ ከመጠየቅ ይልቅ፣ ሂደቱን በአግባቡ መምራቱ የተሻለ ነው:: ስለሆነም፣ ተጠሪ የሆነው መሪ በዕቅዱ ሂደት ላይ መደበኛ ሪፖርት ማግኘት አለበት:: ኮሚቴው በሽማግሌዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ዕቅድ እያዘጋጀ መሆኑን ለማረጋገጥም ከኮሚቴው ሊቀ መንበር ጋር ተቀራርቦ መሥራት አለበት:: ሽማግሌዎችን ስለሚያውቅ ምን እንደሚጠብቁ ይገባዋል:: ስለሆነም፣ ዕቅዶቹ የሽማግሌዎቹን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ እንዲዘጋጁ ለማድረግ ኮሚቴውን መምራት የእርሱ ኃላፊነት ነው::

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ መሪ በኮሚቴው ሥራ ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ዕቅዳቸው በሽማግሌዎች ዘንድ ተቀባይነት ሊያጣ ስለሚችልበት ሁኔታ አንድ ምሳሌ ስጥ:: ለ) ይህ በሽማግሌዎችና በኮሚቴው አባላት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ግለጽ:: |

4. መሪው አስፈላጊውን መረጃ ወቅቱን በጠበቀ መንገድ አይሰጣቸውም:: ጥሩ ዕቅዶችን ለማውጣት፣ ኮሚቴው በቂ ጊዜ ወስዶ መወያየት አለበት:: የኮሚቴው አባላት ዕቅዶቻቸውን ለማውጣት ተገቢውን መረጃ ይፈልጋሉ:: ስለዚህ መሪው ሥራው ከሚጀመርበት ጊዜ ቀደም ብሎ ኮሚቴውን ማዋቀር አለበት:: የኮሚቴው አባላት ዕቅዳቸውን መቼ ለሽማግሌዎች እንደሚያቀርቡ ማወቅ አለባቸው:: ተጠሪ የሆነው ሽማግሌ ለውሳኔ-ሰጭነት አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ሁሉ ቀደም ብሎ መስጠት አለበት::



መጀመሪያ ቡድኑን በሚያዋቅርበት ጊዜ መሪው ሽማግሌዎች ከኮሚቴው የሚጠብቁትን ነገርና ጊዜውም መቼ እንደሚሆን ማሳወቅ አለበት:: ኮሚቴው ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ መረጃ እንደሚያስፈልገው በሚገነዘብበት ጊዜ መሪው መረጃውን በፍጥነት ሊሰጣቸው ይገባል:: ቡድኑ የመገናኘትና የማቀድ ፍላጎት ካጣ እንደገና የዕቅዱን ሥራ መጀመሩ ከባድ ይሆናል:: ለምሳሌ፣ አንድ ጥያቄ ጠይቀው መልሱን የሚያገኙት ከአንድ ወር በኋላ ከሆነ፣ ዕቅድ የማውጣቱ ሂደት ባለበት ይቆማል ማለት ነው:: ጉዳዩ ከተጠሪው የሥልጣን ክልል በላይ ከሆነ፣ ዕቅድ የማውጣቱ ሥራ ይቀጥል ዘንድ በተቻለ ፍጥነት ከሽማግሌዎች መረጃውን ማግኘትና ለቡድኑ መስጠት አለበት::

| |
|---|
| 24ኛ ጥያቄ፡- አንድ ኮሚቴ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ባለመቻሉ ዕቅድ የማውጣት ሥራውን ሲያቆም የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ:: |

5. ኮሚቴው ሥራውን አጠናቅቆ ሽማግሌዎች እንዲያጸድቁለት ሲያስረክብ ሽማግሌዎቹ ምላሽ ሳይሰጡ ይቆያሉ:: ሽማግሌዎቹ ዕቅዱ ተሠርቶ ከቀረበላቸው በኋላ ውጤቱን ለኮሚቴው አባላት መናገር ይኖርባቸዋል:: ዕቅዱ መጽደቁን ወይም የተደረጉ አነስተኛ ለውጦች ካሉም ይህንኑ መግለጽና ለውጥ የተደረገበትንም ምክንያት መናገር ይኖርባቸዋል:: ዕቅዱ በቤተ ክርስቲያን መሪው ጠረጴዛ ላይ ከከረመና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በፍጥነት የማያጸድቁት ከሆነ፣ ሥራውን ያካሄደው ቡድን ተስፋ ይቆርጣል:: «በዚህ ሥራ ላይ ብዙ ደክመናል:: እነርሱ ግን እየት አድርገው ትክክል መሆን አለመሆናችንን ለመናገር አይፈልጉም::» የአንድ ሰው ሥራ በግድየለሽነት ከታየ ወይም እውቅና ካልተሰጠው፣ የወደፊት ተነሣሽነት በከፍተኛ ደረጃ ይዳከማል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ ዕቅዱን በጥንቃቄ አጥንተው ለማጽደቅ ባይችሉ እንኳን፣ ሥራቸው በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው:: ይህም የቡድኑ አባላት ሥራቸው ወደ ጎን ተትቶ እንዳልተረሳ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል::

6. ሽማግሌዎች ለኮሚቴው ክባድ ሥራ ይፋዊ እውቅና አይሰጡም:: ሰዎች ሌሎች ስለ ሥራቸው ምን እንደሚያስቡ ለማወቅ ይፈልጋሉ:: ነገር ግን እግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀምበትን ታላቅ ሥራ ካከናወኑ በኋላ ምስጋናውን ሁሉ ሽማግሌዎቹ የሚወስዱ ከሆነ፣ ሥራውን ያከናወኑት ሰዎች ልብ ያዝናል:: ሽማግሌዎች ምስጋናውን ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን ያደረጉት ሰዎች እንዲቀበሉ ማድረግ አለባቸው::

> 25ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ ዕቅድ የሚያወጣ ወይም ሌላ ተግባር የሚያከናውን ኮሚቴ አባል እንድትሆን ተጠይቀህ ታውቃለህ? ከሆነ፣ የቡድኑ ዓላማ ምን ነበር? ለ) በቡድኑ ውስጥ የመሥራቱ ተሞክሮ ጥሩ ነበር ወይስ መጥፎ? መልስህን አብራራ:: ሐ) ከላይ ከተጠቀሱት ስሕተቶች መሪዎች የፈጸሙት የትኛውን ነበር? መ) ተሞክሮው የበለጠ አስደሳች እንዲሆንልህ መሪዎች ምን የተለየ ነገር ሊያደርጉ ይችሉ ነበር?

## አራተኛ ቀን

**ዕቅዱን በሚያጸድቁበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማጤን አለባቸው:-**

ምንም እንኳን ሽማግሌዎች ራእዩን ለመፈጸም የሚያስችል ዕቅድ ሌሎች ሰዎች እንዲያዘጋጁ ቢጠይቁም፣ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎቶች ለመከታተል ትልቁን ኃላፊነት የሰጠው ለሽማግሌዎች ነው:: ስለዚህ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋና ዋና መርሐ ግብር ማጽደቅ ይኖርባቸዋል:: ሽማግሌዎች አንድን ዕቅድ በሚያጸድቁበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አለባቸው:-

1. የሚቻል ከሆነ፣ እያንዳንዱ ሽማግሌ ከስብሰባው በፊት የዕቅዱን ቅጂ አግኝቶ ቢያነብ መልካም ነው:: ይህም ስለ ዕቅዱ ለማሰብና ለመጸለይ በቂ ጊዜ እንዲያገኝ ያስችለዋል:: ሽማግሌዎች ስለ ዕቅዱ ብዙ በጸለዩና ባሰቡ ቁጥር፣ በስብሰባው ወቅት ጊዜ ሳያጠፉ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ይችላሉ:: ሽማግሌዎች በአዲስ ዕቅድ ላይ በስብሰባ ላይ መነጋገር ቢጀምሩ፣ ስለ ዕቅዱ በጥልቀት ለማሰብና አጥጋቢ አስተያየት ለመስጠት መቸገራቸው የማይቀር ነው:: ብዙውን ጊዜ እንደሚደረገው ሰብሳቢው ዕቅዱን



ያነብና አንዳንድ ሰዎች የመሰላቸውን ይናገራሉ:: የጊዜ እጥረት ስለሚኖር ዕቅዱን አጽድቀውት ያልፋሉ:: ሌሎች አላሳቢ አጀንዳዎች ላይ ለመወያየት በሚደረግ ጥድፍያ፣ በዕቅዱ ላይ ጥልቅ ውይይት ሳይካሄድ ይቀራል:: ጥልቅ ውይይት ካልተካሄደበት ደግሞ፣ ሽማግሌዎች ለአፈጻጸሙ ልባቸውን አይሰጡም:: ይህ የሽማግሌዎች ሳይሆን የኮሚቴው ዕቅድ ይሆናል::

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ የማይፈጽም ዕቅድ ካጸደቁና በተግባር ለመተርጎም ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ፍሬያማ ሊሆን ካልቻለ፣ ጥፋቱ የሽማግሌዎች እንጂ ለመተግበር የሞከሩት ሰዎች ሊሆን አይችልም:: ሽማግሌዎች ሌሎችን መውቀስ የለባቸውም:: ይህ የፈሪ ሰው ሥራ ነው:: ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሥራቸውን በአግባቡ አልተወጡምና:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕቅዱን ለመተግበር ለሞከሩትና ለቤተ ክርስቲያን የራሳቸውን ስሕተት መግለጽ አለባቸው:: ይህ የአመራር «እውነተኛነት» ነው:: ለሥራው ኃላፊነት የተቀበሉ ሰዎች ለውድቀቱ መወቀስ አለባቸው:: ይህም ማለት የሽማግሌዎችን ምክር ካለመቀበል ውጭ ችግሩ የተከሰተው በሽማግሌዎቹ ጥፋት ነው ማለት ነው:: አንድም ዕቅዱ ጥሩ መሆኑን አላረጋገጡም ወይም አስፈላጊውን ክትትል አላደረጉም::

2. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የቀረበውን ዕቅድ ዝርዝር ጉዳዮች መወያየት የለባቸውም:: ይልቁንም፣ ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር ዕቅዱን ይመረምራሉ:-

ሀ. ዕቅዱ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ይፈጽማል? ሽማግሌዎቹ የቀረበላቸው ዕቅድ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ የሚፈጽም መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው:: ካልሆነ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ራእይ ኮሚቴው እንዲቀይር ፈቅዶ እንደ ሆነ ለማረጋገጥ ራእዩን ተመልሰው መከለስ አለባቸው:: ነገር ግን እግዚአብሔር የሚፈልገው አሁንም የመጀመሪያውን ራእይ ስመሆኑ እርግጠኞች ከሆኑ፣ ኮሚቴው ራእዩን በሚፈጽም መልኩ ዕቅዱን እንደገና እንዲሠራ መጠየቅ አለባቸው::